# ምዕራፍ ፳፫

## ነዶ በነዶ ....

ወንጌዊ ኬዳም በጌጃ ቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጤታማ አገልጋይ ከሆኑ ውለው አድረዋል። በአገሪቱ ላይ ያንዣበበው የስደት ወላፈን መጋረፍ ቢጀምርም ወንጌላዊው ግን በርካታ አስፈሪ ፈተናዎችን እያለፉ ወንጌሉን መስበክ ቀጥለዋል። ጌጃ ቃለ ሕይወትም በወንጌላዊ ኬዳሞና በብርቱዎቹ መሪዎቿ የትጋት አገልግሎት ብሎም በእግዚአብሔር ጸጋ በምዕመናንም ሆነ በልዩ ልዩ ዘርፍ በሚያገለግሉ አገልጋዮች መጥለቅለቋ ቀጥሏል። በዚሁ ጊዜ ወንጌላዊ ኬዳሞ እና ወንጌላዊ ከበደ በልሁ ወንበር ላይ እጅ እየጫኑ የጸለዩበት ዘመን ተቀይሮ የእምባቸውን ፍሬ ማየት ከጀመሩ ሰንባብቷል። በጊዜው በርካታ የአዲስ አበባ ቤተ ክርስቲያናት በኮምኒስታዊው መንግስት ተዘግተው በከተማዋ ሳይዘጉ የቀሩት በጣት የሚቆጠሩ የመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያናት እና እንደ ጌጃ ሁሉ ከመዘጋት በተዓምር ያመለጡ ጥቂት የቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ብቻ ነበሩ። ስለሆነም በርካታ የሌሎች ወንጌላውያን አማኝ ቤተ ክርስቲያናት አባላት ለአምልኮ ወደ ጌጃ አጥቢያ ይተምሙ ነበር። ጌጃም የአገልግሎት አድማሷ ሰፍቶ በአስፈሪ የስደት ወላፈን ውስጥ እያለፈች አዳዲስ ነፍሳት እንደቀድሞ ዘመን ሁሉ ዕለት ዕለት ይበዙላት ነበር። በጊዜው የጌጃ መሪዎች እና አገልጋዮች በሦስት ፈረቃ ሕዝቡን ለማስተናገድ በወሰኑት መሠረት የእሁድ አምልኮ ከማለዳው 12 ሰዓት ጀምሮ በየሁለት ሰዓት ልዩነት እስከ 6 ሰዓት ድረስ ይካሄድ ነበር።

በዚሁ ወቅት አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ተጠምተው ከ11:00 ሰዓት ጀምሮ ወደ ጌጃ ቅጥር ግቢ ከሩቅ ሰፍራ ሳይቀር ይመጡ የነበረ ሲሆን የማለዳው አምልኮ በ12:00 ሰዓት ተጀምሮ በ2 ሰዓት ሲጠናቀቅ ወደ ቤታቸው ይመለሱ ነበር።

ከዚህ በመቀጠልም የሁለኛውን ፈረቃ ለመካፈል የሚመጡ ወይም የመጀመሪያውን እንዳይካፈሉ አዳራሹ ጥቅጥቅ ብሎ ሞልቶ የተዘጋባቸው ምዕመናን በቤተ ክርስቲያኒቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሲባጎ ተከልለው በተዘጋጀው ቦታ እንደየ አመጣጣቸው በሰልፍ እየተደረደሩ ተከማችተው ቆመው ይጠብቁ ነበር። የመጀመሪያው የአምልኮ ፕሮግራም እንደተጠናቀቀም የቤተ ክርስቲያኒቱ ዲያቆናት የመጀመሪያውን ረድፍ ታዳሚዎች በሰልፍ አስወጥተው ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ጓሮ ከመሩ በኋላ፣ አዳራሹ ባዶ ሲሆን

*የሁለተኛው ፌረቃ ታዳሚ በታላቅ ጉጉት እና በጥድፊያ ወደ አዳራሹ ያስገቡ ነበር። ይህ የሁለተኛ ፈረቃ አምልኮ የሞላበት ሦስተኛውን ፈረቃ ለመጠበቅ ወደ ሲባኀው ተመልሶ በተመሳሳይ ሂደት ሦስተኛው ፈረቃ አምልኮ ይካሄዳል።*

*በዚሁ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱ ጥቅጥቅ ብላ የምትሞላ ሲሆን ሦስቱም ፈረቃ ተመሳሳይ ዝማሬ እና መልእክት እየቀረበባቸው ሞቅ ያለና እውነተኛ በፊተና ውስጥ ያለፈ አምልኮ የሚካሄድባቸው ነበሩ። የቤተ ክርስቲያኒቱ ዲያቆናትም እነዚህን ሦስት ፕሮግራሞች ቦታ አግኝቶ ለመታደም የሚጓጓ ሕዝብ ለማስተናገድና በወቅቱ የነበረውን የቦታ ጥበት ችግር ለማቃለል በከፍተኛ ትጋት ማገልገል ይጠበቅባቸው ነበር። በአንድ ዕለት በቤተ ክርስቲያን መሰል ፕሮግራም እየተካሄደ ሳለ አንዱ ፈረቃ ተጠናቅቆ ዲያቆናት ሕዝቡን በጥንቃቄ ከአዳራሹ ካስለቀቁ በኋላ ቀጣዩ ፈረቃን ለመካፈል የተሰለፈ ሕዝብ ሲባኀ ተፈትቶለት እየተጋፋና እየተሸቀዳደመ በሩጫ ወደ አዳራሹ ተመመ። በዚህ ጊዜ በሩጫ ወደ አዳራሹ የሄደው ሕዝብ በበሩ ለመግባት ሲገፋፋ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና በር መስታወት በሰዎች ተመትቶ ረገፈ። ይህን የተመለከቱ በዕለቱ አስተናጋጅ የነበሩት አቢይ እና አለማር የተሰኙ ዲያቆናት ተቆጥተው ሕዝቡን በሩ ላይ አስቁመው በኃይል ይገስጹት ጀመር።*

*በዚህ ጊዜ ወንጌላዊ ኬዳሞ በቤተ ክርስቲያኒቱ መድረክ አካባቢ ከአቶ ጥላሁን ኃይሌ ጋር ቆመው ነበር። ኬዳሞ የተፈጠረውን ሁኔታ እንዳዩም በፍጥነት ከነበሩበት ስፍራ ወደ በሩ በሩጫ መጡ። ሁለቱን ዲያቆናትም "በቀበሌ እግዚአብሔር የለም፤ መስሪያ ቤት እግዚአብሔር የለም! እየተባለ እግዚአብሔር አለሁ፤ ብሎ በየግላቸው ነግሯቸው የሰበሰባቸውን ሕዝብ አትናገሩ። ይህ የእምባ ጸሎት ፍሬ የሆነ ሕዝብ ነው። የኛ የጸሎት መልስ የሆነ ሕዝብ ነው። መስታውቱ ይሰበር ነገ እንጠግነዋለን።" ብለው እምባ ባዛለ ንግግር መልሰው ተቆጧቸው። ሕዝቡም ወደ አዳራሹ ገብቶ ፕሮግራሙን ተካፈለ። መስታወቱም በማግስቱ ተገጠመ።*

---------------------//--------------------

የጌጃ አጥቢያ በብዙ አማኞች ሳትሞላ በፊት እኔ በመጣሁበት ጊዜ ጥቂት አባላት ብቻ ነበሯት። እኔና ከበደ በልሁም ከእሁድ አምልኮ አስቀድመን በየወንበሩ ላይ እጅ እየጫንን ጌታ ሰው እንዲልክ ስንጸልይ ቆይተናል። ነገር ግን ይህ ወንጌል እንዲስፋፋ የነበረን ጥማት በዚህ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። ይልቁንም እኔ ገና ወደ ጌጃ ስመጣ በተሰጠኝ የሥራ ዝርዝር መሠረት ወንጌልን ማዳረስ አንዱ ሥራዬ ነበር እና ወንጌልን የማሰራጫ ስልት ነደፍኩ። በዚህም መሰረት ገና ስጀምር ለ14 አዳዲስ አባላት የወንጌል ስርጭት ስልጠና ሰጥቼ ወደየ አካባቢያቸው አሰማራኋቸው። ወዲያውኑ ቁጥራቸው ጨምሮ ሃያ ሆነ። ይህ ቁጥር እየጨመረ ሄዶ ከትንሽ ጊዜ ቆይታ በኋላ 180 የወንጌል መስካሪዎች አሰልጥኜ አሰማርቼ ትልቅ የወንጌል ስርጭት እናካሂድ ነበር።

ከጥቂት የቆይታ ዓመታት በኋላም የጌጃ አባላት ቁጥር 212 ስለደረሰ ያለንን የአገልጋዮች ብዛት ከግምት በማስገባት በደንብ ተዘጋጅተን በዓመት ብቻ 1000 ሰው

ወደ ጌታ ለማምጣት እቅድ ነደፍን፡፡ በእቅዳችን መሰረትም የሰለጠኑ አገልጋዮች ሁሉ ለ4 ሺህ ያህል ሰው ወንጌል እንዲመሰክሩ እያደረግን ነበር፡፡

ይህ የወንጌል ሥርጭት አገልግሎታችን ውጤታማ ስለነበረም አዳዲሶቹን አማኞች የደህንነት እና የጥምቀት ትምህርት በመቀጠልም የቤተ ክርስቲያናችንን የእምነት አቋም እያስተማርን በየሦስት ወሩ ልዩነት (በዓመት አራት ጊዜ) የጥምቀት ሥርዓት እናካሂድ ነበር፡፡

በዚሁ ወንጌል የመስበክና ያመኑትን የማስተማር አገልግሎታችን ሂደትም ብዙ ሳንካ ያጋጥመን ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ካድሬዎች የምናደርገውን ለማየት አመንን ብለው ይመጡ እና የጥምቀት ትምህርት ተምረው አጠናቅቀው ፈተና አልፈው ለመጨረሻ ጥያቄ እኔ ጋ ቀርበው የነበሩባቸውን አጋጣሚዎች አስታውሳለሁ፡፡

አንድ ጊዜ አብነት አካባቢ የምትኖር አንዲት ወጣት የጥምቀት ትምህርት ተምራ አጠናቅቃ እኔ ጋ ለመጨረሻ ጥያቄ ቀርባ ነበር፡፡ እኔም "እንዴት ጌታን ተቀበልሽ? ለምን በክርስቶስ አመንሽ? ከተጠመቅሽስ በኋላ ምን መሆን ትፈልጊያለሽ?" ብዬ ጠየቅኋት፡፡ በዚህ ጊዜ ልጅቱ በልቧ ውስጥ የታመቀውን ምስጢር ገልጣ፡-

"ከተጠመቅሁ በኋላ እዚሁ ሥራ ለመቀጠር ነው የምፈልገው፤ ሥራ የለኝም፡፡" አለችኝ፡፡ በኋላ እኔም ሳታምን የጥምቀት ትምህርት ስትማር የኖረችው ሥራ ለማግኘት መሆኑን ስትነግረኝ በዚህ ሁኔታ መጠመቅ እንደማትችል እና እኛ ይህንን ሁሉ የምናካሂደው ለሥራ ፈላጊዎች የሥራ በር ለመፍጠር እንዳልሆነ፣ የሚጠመቁ ሰዎች ጌታን ሲቀበሉ በእውነተኛ እምነት ነፍሳቸውን ለማዳን የሚያደርጉት እንደሆነና እምነት ካላቸው ብቻ የጥምቀት ትምህርቱን ተምረው እንደሚጠመቁ ቤተ ክርስቲያንም ለሥራ ፈላጊዎች እንዳልተቋቋመች አስረድቼ ከጥምቀት ሥርዓቱ አስወጣኋት፡፡

ልጅቱም በመጨረሻ ይህንን ሁሉ እንደማታውቅ እና ሥራ ለማግኘት ብቻ ብላ እንደተመላለሰች አምና የደህንነትን መንገድ እንደገና "ሀ" ብላ ተምራ ጌታን ተቀብላ በእምነት የጥምቀት ትምህርት በመማሯ ከዚያ በፊትም የነበራት መንፈሳዊ ያልሆነ ባህርይ ተለወጠ፡፡ ከዚያም ተጠምቃ የቤተ ክርስቲያን አባል ሆና ትዳር ከመሰረተች በኋላ አሁን ወደ አሜሪካን አገር ሄዳለች፡፡

በዚህ ዓይነት አሁን ልዘረዝራቸው ከምችላቸው በላይ የሆኑ ሰዎች ከተለያየ የሕይወት መስክ እየመጡ ጌታን ይቀበሉ እና የዘላለም ሕይወት ያገኙ ነበር፡፡ እኔንም እግዚአብሔር ከገጠር አውጥቶ ብዙ የተማሩ ሰዎችን ወደ ራሱ እንዳሰባስብ ተጠቀመብኝ፡፡

አንድ ጊዜ አንድ በጣም የጠለቀ መንፈሳዊ እውቀት ያለው የኦርቶዶክስ ክርስትና አማኝ የነበረ እና የቤተ ክህነት ትምህርት ያለው ሰው አምና ወደ እኛ መጣ፡፡ እኔ የሰውየውን ሁኔታ እና ያለውን እውቀት በማየት ለብዙ ወራት ከሌሎች የደህንነት ትምህርት

ተማሪዎች ለይቼ አስተማርኩት። ያ ሰውም በሳል ሰው ስለነበር በመንፈሳዊ ሕይወቱ በሚገባ ጠንክሮ ጌጃ ቆይቶ የቦሌ አጥቢያ ቃለ ሕይወት ስትከፈት ወደዚያው በማምራት ለረጅም ዓመታት በዲያቆንነት ሲያገለግል ቆይቶ አሁን በአሜሪካ በመኖር ላይ ይገኛል።

ልክ እንደዚህ ሰው ከአድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን የመጣና ዛሬ በቦሌ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በአንድ ከፍተኛ የአገልግሎት ዘርፍ ላይ የተሰማራ ወንድም ነበር። እርሱም ወደ እኛ ከመጣ በኋላ ቀደም ሲል በአድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን እያለ ተምሮ ስለተጠመቀ በቀጥታ የእኛ አባል ሆኖ መቀጠል ስለፈለገ "ቀድሞ ስለተጠመቅኩ አባል መሆን እችላለሁ ወይ?" ብሎ ሲጠይቀኝ "ዝም ብለህ ትምህርቱን ተማር እና ከዚያ በኋላ ትወስናለሁ" አልኩት።

ከዚያም አምስት ተከታታይ የደህንነት፣ ሃያ ተከታታይ የጥምቀትና በመጨረሻም የቤተ ክርስቲያናችንን የእምነት አቋም አስተምሬው ከጨረስን በኋላ ራሱ መጠመቅ እንዳለበት ወስኖ በመጠመቅ የቤተ ክርስቲያናችን አባል ሆነ። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር እየረዳን ብዙዎች እያመኑ ጠንካራ ደቀ መዝሙር ይሆኑ ጀመር።

በቤተ ክርስቲያን ላይ የነበረው ስደት እየበረታ መጥቶ በመጀመሪያ እነ ሙሉ ወንጌል በመቀጠል መሠረተ ክርስቶስ፣ ገነት እና ሌሎችም ቤተ ክርስቲያናት በመዘጋታቸው በዚህ ጊዜ የእነዚህ ቤተ ክርስቲያናት አገልጋዮች እና አባላት እኛጋ መጥተው ማምለክና መገልገል ጀመሩ።

እኔም የቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ተዘግቶ በህንጻው አጠገብ ባለፍኩ ቁጥር በርካታ አባላት እኛጋ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚማሩ እና ቅርበት ስለነበረን በጣም አዝን ነበር። ሁል ጊዜም በዚያ አካባቢ ሳልፍ "እግዚአብሔር ሆይ እንዴት አይተህ ዝም አልክ? ምንም ዓይነት ድካም ቢኖር ምህረትህ ወዴት ሄደ?" እያልኩ እየጠየቅሁና ልቤ እየተቃጠለ ነበር የምሄደው። ከዚህ የተነሳም እኛ ከሌላ ቤተ ክርስቲያናት የመጡትን በፍቅር ተቀብለን ለመያዝ እንጥር ነበር። አማኑኤል አካባቢ የነበረችው የገነት ቤተ ክርስቲያንም እኔን ልክ እንደራሷ ወንጌላዊ ነበር የምትቆጥረኝ። ብዙ ጊዜ ወደዚያ እየሄድኩ አስተምር ስለነበር አባላቱም እኔን እንደ ራሳቸው አገልጋይ ያዩኝ ነበር። የእነርሱ ቤተ ክርስቲያን በተዘጋች ጊዜም ሁሉም በቀጥታ ወደ ጌጃ መጥተው ነበር። በዚሁ የመዘጋት ጉዳይ ላይም ከእነርሱ ጋር ሆነን ለብዙ ጊዜያት እያለቀስን ጸልየናል።

በመጨረሻም ያ ዘመን አልፎ የእምነት ነጻነት ሲታወጅና ቤተ ክርስቲያናቱ እንደገና ሲከፈቱ ሁሉም በሚያዘጋጁአቸው የምስጋና ፕሮግራሞች እየጋበዙኝ አገለግያለሁ። በሰፈረ ገነትና በሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያናት በተዘጋጁ የምስጋና ፕሮግራሞች ላይ እየተገኘሁ የእግዚአብሔርን ድንቅ አድራጊነት ሰብኬአለሁ። የእነዚህ ቤተ ክርስቲያናት አባላት በዚያ ዘመን የኛ አባላትን ሁሉ እየቀደሙ ለአምልኮ ጌጃ ይገኙ ነበር።

የቤተ ክርስቲያናችን የሦስት ፈረቃ የእሁድ አምልኮ በሽማግሌዎች እንዲጀመር የተወሰነው እነዚህ ቤተ ክርስቲያናት በመዘጋታቸው ምክንያት ነበር። እግዚአብሔር በዚያ ክፉ ዘመን እኛን የብዙ ወገኖቻችን መጠለያ ለመሆን ስላበቃን ስሙ ይክበር።

በእነዚያ አስገራሚ ዓመታት ወቅት የነበረውን ጊዜ ሳስታውስ በጣም የሚያስገርመኝ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለአምላኩ የነበረው ፍቅር ነው። ያኔ ለሠራነው የተጠናከረ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ብዙ ሰው ፈቃደኛ ሆኖ ራሱን እየሰጠ ያገለግል ነበር። ሕዝቡ የአምልኮ ፕሮግራም ለመካፈል የነበረው ጥማትም እጅግ ያስደንቅ ነበር። እሁድ በማለዳ ከ 11:00 ሰዓት ጀምሮ እንዲሁም የምሽት አምልኮ ከተዘጋጀም ህዝቡ መጥቶ ቤተ ክርስቲያኒቱን ይሞላል። ያኔ እግዚአብሔርን ማምለክ እንደዛሬ አልረከሰም ነበር።

በዚህ ዘመን ምዕመኑ በፈለገበት ሰዓት መጥቶ ማምለክ እንደሚችል ስለሚያስብ በፈለገው ሰዓት ሁሉ ለመምጣት ተረጋግቶና አርፍዶ ነው የሚደርሰው። በዚያ ዘመን ግን ከስደቱ የተነሳ በየቦታው በሩ ስለተዘጋ ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን ይተጋ ነበር።

## ያመኑትን ማሳደግ

በዚያን ዘመን ወንጌል ሰብከን ሰዎችን አባል ማድረግ ላይ ብቻ አናተኩርም ነበር። በአገልግሎቱ የማተኩርባቸው ሦስት ነገሮች ወንጌልን መስበክ፣ ያመኑትን ማስተማርና የበሰሉ ተተኪ አገልጋይ ክርስቲያኖች ማድረግ ላይ ነበር። በዚህ ዓላማችን መሰረትም ያመኑትን (ከ20-30 የሚሆኑትን) በአንድ ላይ የደህንነት እና የጥምቀት ትምህርት በተለያዩ አስተማሪዎች አስተምረን ስንጨርስ ያስተማራቸው ሰው ፈትኖ ማለፋቸውን ያረጋግጣል። ከዚያም ወደ ጥምቀት ከመሄዳቸው በፊት ወደ ሽማግሌዎች ይቀርቡ እና ከሽማግሌዎች ጋር እያንዳንዳቸውን እናነጋግራቸዋለን።

ይህንን ሁሉ ሂደት በማለፍ አንድ አማኝ ተጠምቆ የቤተ ክርስቲያናችን አባል ከሆነ በኋላ ደግሞ ለአባላት የተዘጋጀ ትምህርት ወደሚማርበት ኅብረት ይሸጋገራል። በጊዜው በሐዋርያት ሥራ፣ በዮሐንስ ወንጌል፣ በሮሜ እና በመሳሰሉት መጻሕፍት ላይ የተዘጋጁ በአንድ ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቁ እና በየሦስት ወራቱ የሚሰጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጻሕፍት ነበሩ። በአንድ ቡድን ውስጥ አምስት ሰው ብቻ የሚመደብባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ የጥናት ቡድኖች ይቋቋማሉ። በእነዚህ ቡድኖች አማካኝነትም ጥናቱ በሳምንት ውስጥ በተመደበለት ጊዜ እና ሰዓት በቋሚነት ይካሄዳል። በዚያ ዘመን በአዲስ አበባ ከተማ በልዩ ልዩ ስፍራዎች በእኛ አባላት ብቻ የሚካሄዱ ከ100 በላይ የጥናት ቡድኖች ነበሩን።

ወንጌላውያን እነዚህን ልዩ ልዩ የጥናት መምሪያዎች አዘጋጅተን ለሽማግሌዎች እናቀርብና ታይቶ አገልግሎት ላይ ይውላል። በዚህ አገልግሎት ውስጥ በጣም

..ጋሬያችን እና አጋጥሮችን የነበረው አቶ ጥላሁን ኃይሌ ነበር። አቶ ጥላሁን አንድ እቅድ ሲቀርብለት ቶሎ የሚቀበል ሰው አይደለም። ብዙ ጥያቄ ያነሳል። "ለምን አስፈለገ? እንዴት ሊፈጸም ይችላል? እንዴት ይቀጥላል?" በማለት ብዙ ይጠይቃል።

አንድ ጊዜ ካመነበትና ከተቀበለ በኋላ ግን በሙሉ ልቡና ኃይሉ እያገዘ ሠርቶ የሚያሠራና ሥራ እንዴት መሠራት እንዳለበት የሚያውቅ ትጉህና ታታሪ መሪ ነበር።

እዚህ ጋ ስለ አቶ ጥላሁን ትንሽ መናገር እሻለሁ። አቶ ጥላሁን ያኔ በኛ ቤተ ክርስቲያን ካሉት በጣም የተሰጡ መሪዎች አንዱ እና በብዙ ትጋት የሚያገለግል ወንድም ነበር። በተለይ ከቤተ ክርስቲያን የጠፉ (የቀሩ) ሰዎችን ፈልጎ በማግኘት ማንም የማይስተካከለው ትልቅ አገልጋይ ነበር። ዛሬ በአዲስ አበባ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት የአቶ ጥላሁንን ዓይነት ሥራ የሚሠራ ሰው ፈጽሞ አልተነሳም። ይህንን ሳስብም ልቤ በጣም ያዝናል።

እኔ ጌጃን ካወቅሁበት ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን የነበራት አንድ ትልቅ ልማድ በየዓመቱ ለአንድ ወር የሚቆይ ትምህርታዊ ኮንፈረንስ ማዘጋጀት ነበር። ይህ ኮንፍራንስ ሲዘጋጅ ከጌጃ ቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጪ ባለ የተለየ ስፍራ የሚዘጋጅ ሲሆን በአብዛኛው በመካነ ኢየሱስ ሴሚናሪየም ይካሄድ ነበር፤ አንድ ጊዜም ላንጋኖ ሄደናል። ይህ ኮንፍራንስ ሲዘጋጅ የጌጃ አባላትና ሕጻናት (ልጆቻቸው እንኳን ሳይቀሩ) ሙሉ ፕሮግራሙን ይካፈሉ ነበር። በዚያ ዘመን ክርስቲያኖች ከየትኛውም ጉዳይ የሚቀድም ጉዳያቸው ክርስትናቸው እና ኅብረታቸው ነበር። ያኔም (በተለይ በላንጋኖ በተካሄደው ፕሮግራም ጊዜ ወቅት) መኪና ዋናው መንገድ ዳር ሲቆም ሕዝቡ ሁሉ ሴቶቹም ዕቃቸውን ተሸክመው በዚያ አድካሚ መንገድ እንዴት ተንገላትተው እንደደረሱ ዛሬም ድረስ በዓይነ ህሊናዬ ይታየኛል።

ላንጋኖ በነበረን ቆይታም እነ ወተቴ እንደሻው፣ አልማዝ በቀለ፣ ቀለሚ ኃይሌ፣ ቆንጂት ዲኬ፣ ... የመሳሰሉ እህቶች ምግባችንን እያዘጋጁ ትምህርቶቹንም በትጋት እየተማሩ በብዙ ዋጋ የሚከፍሉ ጠንካራ አገልጋዮች ነበሩ።

እኔ እና የአገልግሎት አጋሬ የሆነው ከበደ በልሁም ብዙ ኃላፊነቶችን ተሸክመን እናስተባብር ነበር። ከበደ በልሁ በጣም ትጉህ እና ፈጣን ደግሞም ብሩህ አዕምሮ የነበረውና በሁሉ አቅጣጫ የሚዘረጋ ሰው ነበር። ለእኔ ተገቢውን አክብሮት በመስጠት ዝቅ ብሎ የሚታዘዘኝ ጥሩ የአገልግሎት አጋሬ ስለነበር የእርሱን የዚያ ዘመን ትጋት እስከ ዛሬ ድረስ አስታውሳለሁ። ከበደ በኔ የመጀመሪያ የአገልግሎት ዓመታት አብሮኝ ሲያገለግል ቆይቶ ብዙም ሳይቆይ ተለይቶን ከአገር ወጥቶ ነበር፤ በመጨረሻም ውጪ አገር እያለ ነፍሱ ወዳገለገለው ጌታ ተሰብስባለች።

በእነዚያ የአንድ ወር ዓመታዊ ኮንፍራንሶቻችን ላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች በአጠቃላይ በጋራ ሆነን ያሳለፍነውን ዓመት የሥራ ክንውን በመገምገም በመጪው

ዓመት አገልግሎት ላይም እናቅዳለን። ለቤተ ክርስቲያን ምን ትምህርት እንደሚያስፈልግ ታስቦ እና ተጸልዮ በመጪው ዓመት ስለሚሰጠው ትምህርት በማመን መቼ መስጠት እንዳለበትም ይወሰንና ይታቀድ ነበር።

በዚህ ዓይነት በጥንቃቄ፣ በትጋት እና በፍጹም አንድነት እየሠራን ጌጃ መሠረተ ሕይወት በብስለትም ሆነ ተተኪ አገልጋዮችን በማፍራት በሦስቱም አቅጣጫ እንደሚገባ ልታድግ በቅታለች። እግዚአብሔር ይመስገን።

በዚያ የሶሻሊስት መንግስት ዘመን አስፈሪ፣ በነበረው ወታደራዊ አገዛዝ በቡሪያችን ብዙ አደጋ ቢያንገርብብም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆኖ ስለሠራ ነዶ በነዶ እየሆንንና ብዙ ምርኮም እናገኝን ነበር። ጌጃ ከነበረን ፍሬአማነት ባሻገርም በብዙ አቅጣጫ እግዚአብሔር ድልን ይሰጠን ነበር። ከእነዚህም ድሎች አንዱን በዋቢነት አንስቼ ልተርክ እሻለሁ።

ጊዜው ልክ አጼ ኃይለ ሥላሴ ከመንበረ ስልጣናቸው የወረዱበት እና የአገራችን የፖለቲካ ትኩሳት በጣም የተጋጋለበት ነበር። እኔም ምንም እንኳ ለአዲስ አበባ ኑሮ አዲስ ብሆንም ለወንጌል አገልግሎት አዲስ አልነበርኩም። የአገልግሎት በር ሲከፈት ወደተለያዩ አካባቢዎች እየሄድኩ አስተምር እና አገለግል ነበር። በዚህ ሁኔታ እያለንም የቤተ ክርስቲያናችን ቀደምት ሽማግሌ እና እኔ ወደ ጌጃ እንድዛወር ከጠሩኝ መሪዎች አንዱ የሆኑት አቶ ላቀው በሚኖሩበት ጎፋ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ አቶ ጌታቸው ክ/ማርያም በሚባል ትጉህ ወንድም ቤት ቅዳሜ ቅዳሜ ሰዎች እየተሰበሰቡ አስተምር ነበር። ይህንን ትምህርት ሰዉ እየወደደው ተጠራርቶ ስለመጣ የሚካፈለው ሰው ቁጥር እየጨመረ መሄድ ጀመረ። እኔም በዚህ ዓይነት ከመኖሪያ ቤቴ እየተመላለስኩ ከአንድ ዓመት በላይ ሳስተምር በመቆየቴ የነበረው ኅብረትም እየጠነከረ ሄደ።

ልክ በዚህ መልኩ እየቀጠልን እያለም በወሎ ክፍለ ሀገር የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩት የወንድማማች ቤተ ክርስቲያን መስራች ሚስዮናውያን ይህንን ኅብረት መጥተው ይካፈሉ ጀመር።

ከተወሰነ ጊዜ ቆይታ በኋላም እኔ በማስተማር አቶ ጌታቸው ክ/ማርያም ደግሞ በማስተባበር ስናገለግለው የቆየነውን ኅብረት ሚስዮናውያኑ የራሳቸው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለማድረግ ፈለጉ። ይህንኑ ፍላጎታቸውንም ለቤተ ክርስቲያናችን መሪዎች ጥያቄ አድርገው አቀረቡት። የጌጃ መሪዎችም ኅብረቱ የወንድማማች ቤተ ክርስቲያን የጎፋ አጥቢያ ሆኖ እንዲመሰረት ፈቀዱ። እኔም በዚያ ስፍራ ስሰጥ የቆየሁት አገልግሎት አዲስ ቤተ ክርስቲያን በመትከል በፍሬያማነት ተጠናቅቆ ወደ ቀጣዩ አገልግሎቴ አመራሁ።

# ምዕራፍ ፳፬

# ከሰማርያ ወደ ዓለም ዳርቻ የመዘርጋት ጅማሬ

# (ኬንያ)

*ወንጌላዊ ኬዳሞ የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል በፍቅር ተሸክመው ለመዘርጋ ቃል ከገቡ ጀምሮ እግዚአብሔር በሳካቸው ምድር ሁሉ በታማኝነት ለወንጌሉ ዓላማ ብቻ እየኖሩ ለብዙዎች መዳን፣ መታነጽና የወንጌሉን አደራ ተረክቦ መሰማራት ምክንያት ሆነዋል። እግዚአብሔርም የአገልግሎት አድማሳቸውን ዕለት ዕለት እያሰፋ ከሻሸጎ በበቅሎ ወደ ቦቢቾ፤ ከቦቢቾ በመኪና ወደ አዲስ አበባ አሻግሯቸው የአዲስ አበባ ከተማ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆነዋል። የሚታመኑበትና ታማኝ የሆነ አምላካቸውም የአገልግሎት ካስማቸውን አስፍቶ እንደገና ከመኪና ወደ አውሮፕላን ተሻግረው ከኢትዮጵያ ውጪ ሄደው የሚያገለግሉበትን ዘመን አመጣ።*

*በ1976 ዓ.ም በኬንያ ያሉ ኢትዮጵያውያን ኬዳሞ ኬንያ ሄደው እንዲያገለግሏቸው የጥሪ ደብዳቤ ላኩ። ሆኖም ነገር ሁሉ በጠበበት በዚያ ከባድ ዘመን በህጋዊነት አገሪቱን እየመራ ካለው መንግስት ርዕዮተ ዓለም ጋር የማይሄድ ዓላማ ይዞ ለሚነሳ ሰው የጉዳዩ መሳካት እጅግ አጠራጣሪ ነበር። ብዙዎችም ከአገር ለመውጣት ብዙ ተገቢነት ያለው ሰነድ አቅርበው እየተከለከሉ ቀርተዋል። ኬዳሞም ከኬንያ በመጣው የአገልግሎት ጥሪ መሰረት ፈቃድ ሊጠይቁ ወደሚመለከተው የመንግስት ቢሮ ባመሩበት ወቅት እንደተለመደው የጥያቄ መዓት ቀረበላቸው። "ለምን? በምን ምክንያት? እንዴት? እና ማን ጋ ትሄዳለህ?" የሚሉ ጥያቄዎችን በተከታታይ መለሱ። በተለይም ዋነኛውን የጉዞአቸውን ዓላማ አስመልክቶ ብዙ ተጠየቁ። ወንጌላዊውም እንደልማዳቸው ምንም ሳያድበሰብሱ "ለአገልግሎት ተጠርቻለሁ" ብለው ተናገሩ። ኃላፊዎቹም መልሳቸውን ሰሙ እና "አንተ እውነት ስለተናገርክ ሂድ።" ብለው የይለፍ ፈቃድ ተሰጣቸው።*

*ይሁንና ወንጌላዊው የኬንያውን ጉዞ ዝግጅት በማጠናቀቅ አስፈላጊውን መስፈርት ሁሉ አሟልተው ዕቃቸውን ሸክፈው ከተነሱ በኋላ እርሳቸው በውል ባልገባቸውና*

*ከአውሮፕላን ጋር እንደተያያዘ በተነገራቸው ምክንያት የዚያ ዕለት በረራቸው ተሰርዞ ወደ ቤታቸው ተመለሱ። በጊዜውም አስቀድመው ፕሮግራም ባደረጉት መሰረት የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና አገልጋዮች የዘጋጁት እና የመተናነጽ ጊዜ ለመውሰድ ወደ ባቦጋያ ይጓዙ ነበር። ኬዳሞም ቀጣዩ የጉዞ ሁኔታ እስኪመቻች ከጌጃ ወገኖች ጋር አብረው ወደ ባቦጋያ አመሩ።*

*በጊዜው የኬንያው ጉዞ በመስተጓጎሉ ቅሬታ ተሰምቷቸው ስለነበር ባቦጋያ እንደደረሱ በግላቸው በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክከው ጸለዩ። ጸሎታቸውን አጠናቅቀው ሲነሱም እግዚአብሔር ጉዞአቸውን ያስተጓጎለው ለመልካም እንደሆነ በግልጽ ተናገራቸው።*

*ኬዳሞም ስለ ጉዞአቸው ከሚያውቁት የወቅቱ የጌጃ መሪዎች አንዱ ለነበሩ ለአቶ ጥላሁን ኃይሌ ከእግዚአብሔር የሰሙትን ተናገሩ። በጊዜው ባቦጋያ ሀይቅ ዳርቻ ባለ ሜዳ ላይ እየተዝናኑ የነበሩትን አቶ ጥላሁን ኃይሌን ተጠግተው "ከኬንያ ስለቀረሁ አዝኜ ነበር። አሁን ስጸልይ ግን ነገሩ ለበጎ እንደሆነ እግዚአብሔር ትክክለኛ መልስ ሰጠኝ።" አሏቸው። ወዲያውም ኬዳሞ ይህንኑ ሃሳብ ሊያጋሩ እና በሌሎች ጉዳዮች ላይም ሊጨዋወቱ ወደ ሌሎች ዘወር ሲሉ አቶ ጥላሁን ኃይሌም እዚያ ሜዳ ላይ በጊዜው ይዘዋት የነበረችውን ትንሽ ሬድዮ እየጎረጎሩ ቆዩ። ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላም አቶ ጥላሁን ወደ ሬድዮው እያመለከቱ ኬዳሞን ይጣሩ ጀመር። "ኬዳሞ... ኬዳሞ ስማ። አንተ እንዳልከው ጉዞህ መሰረዙ ለመልካም ነው።" እያሉ በጣም ይደሰቱ ገቡ። አቶ ጥላሁን በሬድዮ ሰምተው የተደነቁበትና የተደሰቱበት ዜና በጊዜው በኬንያ ትልቅ ብጥብጥ ተነስቶ ብዙ ሰው እንደሞተ እና ብዙ ሱቆች እንደተዘረፉ በመገናኛ ብዙኃን መዘገቡ ነበር። በዚህ መልኩ እግዚአብሔር አገልጋዩን በማያውቁት አገር ሊያጋጥማቸው ከነበረ አደጋ እና ሁከት ታደጋቸው።*

............................//............................

የኬንያ ጉዞዬ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር አስደናቂ ጥበቃ ከክፉ ሊጋርደኝ ቢስተጓጎልም ግን ከነ ጭራሹ አልቀረም ነበር። ስለሆነም መጋቢት ወር ጉዞው ተስተጓጉሎ ቀርቼ ብዙም ሳልቆይ በግንቦት ወር ላይ ሁኔታዎች ተመቻችተው ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢትዮጵያ ወጥቼ በሌላ አገር ለማገልገል በቃሁ።

እግዚአብሔር ረድቶኝም በኬንያ ቆይታዬ ያለ ዕረፍት ያገለገልኩበት ውጤታማ ጊዜ ሆነልኝ። ሁል ጊዜ ሰኞ ብቻ እረፍት አደርግ የነበረ ሲሆን በተቀሩት ቀናት ሁሉ ግን ኬንያ ያሉ ኢትዮጵያውያንን አገለግል ነበር። በየፕሮግራሙ ላይ ልዩ ልዩ የደህንነት መልዕክቶችን ጨምሮ በመሰረታዊ የክርስትና ሕይወት ላይም ከኤፌሶን መጽሐፍ ተከታታይ ትምህርት አስተምራያለሁ። በመጨረሻም የቆላስያስን መጽሐፍ አስተምሬአቸው ነበር።

በኬንያው ቆይታዬ ሚ/ር ብራንት የሚባሉ ፈረንጅ አብረውኝ ያገለገሉ ሲሆን ያሳለፍኳቸውን ጊዜያትም የኖርኩት በእኚህ ሰው ቤት እና ጌጃ አብረውኝ በነበሩት አቶ ብርሃኑ ደረሰ ቤት ነበር። በመጨረሻም አቶ ብርሃኑ ወደ ኢትዮጵያ ስመለስ አብሮኝ መጥቷል።

ኬንያ በቆየሁበት ጊዜ በዚያ ዘመን ከነበረው ስደት የተነሳ ከአዲስ አበባ ኮብልለው የሄዱ በርካታ የማውቃቸውን ኢትዮጵያውያን አግኝቻለሁ። እንደውም በሄድኩ ማግስት ከአቶ ብርሃኑ ደረሰ ልጅ ጋር ከተማውን ለማየት እየተዟዟርን እያለ በድንገት በመንገድ የሚያልፉ የቀድሞ የኔ ተማሪዎች አግኝተውኝ ሳንጋብዝህ አንለቅህም ብለው ናይሮቢ ከተማ ውስጥ ትልቅነቱ ወደሚታወቀው ኬንያታ ሆቴል ወስደው ጋብዘውኝ ተለያየን።

ኬንያ በነበረኝ አጭር ቆይታ አንድ ነገር ለማስተዋል ችዬ ነበር። እዚያ የነበረኝን የአገልግሎት ጊዜ እንደጨረስኩ እነ አቶ ብርሃኑ ለአንድ ሳምንት ያህል "ለምን ሞምባሳ ሄደህ አታርፍም?" የሚል ሃሳብ አቀረቡ። በጊዜው እነርሱ ይህን ሃሳብ ያቀረቡት እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለብኝን የአገልግሎት ጫና እና በአዲስ አበባ እና በልዩ ልዩ ቦታዎች እየተዘዋወርሁ እንደማገለግል ስለሚያውቁ ነበር። እነርሱ ጋ በቆየሁባቸው ሁለት ሳምንታትም ቢሆን ያለ እረፍት ማገልገሌን አይተዋል። ስለሆነም ሀሣባቸው ወደ አዲስ አበባ ከመመለሴ በፊት እረፍት አግኝቼ እንድሄድ ነበር።

እኔ ግን ልቤ ፈጽሞ ኬንያ የመቆየት ፍላጎት አልነበረውም። እንዲያውም ኢትዮጵያ ያለውን እና በአስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ የሕዝቡን በትጋት እግዚአብሔርን ለማምለክ የመሰባሰብ ባህል አስታውሼ ቶሎ በመመለስ በዚያ ሕዝብ መካከል መገኘት ናፈቀኝ። የኬንያውን የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ከኢትዮጵያው ጋር ሳመዛዝን አንድ የታዘብኩት ክስተት ትዝ አለኝና ነገርኳቸው።

አዲስ አበባ በሚገኘው የመኖሪያ ቤታችን እኔና ልጆቼ በበጋ ወራት በግቢአችን ያሉ አትክልቶችን የውሃ ማጠጫ ጎማ ከቧንቧ ጋር አስረን ውሃ እናጠጣ ነበር። ውሃውን በጎማው ወደ ተለያዩ ቦታዎች ለማዳረስ እንድንችልም በተለይ ራቅ ወዳለ ቦታ እንዲሄድልን የጎማውን ጫፍ በጣታችን እናፍነዋለን። በዚህ ጊዜ ውሃው በኃይል ተስፈንጥሮ ይወጣና ወደምንፈልገው አቅጣጫ ረጅም ርቀት ይሄዳል።

እኔም ይህን ታሪክ ለኬንያ የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነገርኳቸው እና "በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ልክ እንደዚህ ዓይነት ጣት አለ። ይህ ጣት የመከራ እና የስደት ጣት ነው። ህዝቡ በስደት እና በመከራ ውስጥ ቢሆንም ያ ጣት ልክ እንደ ውሃው ለህዝቡ የጸሎት እና የአገልግሎት ኃይል ይጨምራል። ይህም ለኔ እግዚአብሔር በዚያ ስፍራ እንዳለ ያሳየኛል። እዚህ ያለውን ሁኔታ ግን ውሃው ሲለቀቅ ዝም ብሎ እንደሚፈሰው ዓይነት አድርጌ አየዋለሁ" ነበር ያልኳቸው።

"እናንተ እዚህ ተዝናንታችሁ ስለምትኖሩ ከእግዚአብሔር ጋር የያዛችሁትን ቀጠሮ እንኳን በደንብ አክብራችሁ አትመጡም። ሁል ጊዜ ተዝናንታችሁ አርፍዳችሁ ነው የምትመጡት። በኢትዮጵያ ግን ገና ሳይነጋ በማለዳ የጸሎት ቤቱ በህዝብ ግጥም ብሎ ይሞላል። እኔ እዚያ እግዚአብሔር ባለበት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር አብሬ መሆን ስለምፈልግ ቶሎ ብመለስ ይሻለኛል።" ብዬአቸው ወዲያውኑ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ። ሁል ጊዜ እግዚአብሔር ባለበት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መሆን ከምንም በላይ የተሻለ ነው።

# ምዕራፍ ፳፫

# መብዛት

## የሰናፍጪ ቅንጣት ....

*በጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አስፈሪዎቹ የጭንቀት ዓመታት አልፈው የቤተ ክርስቲያን መዘጋት እና የአገልጋዮች መታሰር ስጋት ተወግዷል። የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም በከፈተችው አገር አቀፍ ቢሮ አማካኝነት ከመንፈሳዊ ሥራዎቿ ጎን ለጎን በርካታ ልማታዊ ሥራዎችን በመሥራት በብሔራዊ ደረጃ አስተዋጽኦ የምታበረክት ሆናለች። የጌጃ መሪዎችም አንዳንዶቹ ባሉበት ሲቆዩ ሌሎቹ ደግሞ ከምኒስታዊው መንግስት ሳይቀር አስገዳጅ ሆኖበት በልዩ ልዩ ረጂዎች በተጀመሩት የልማት እና እርዳታ ቢሮዎች (የቃለ ሕይወትን ጨምሮ) እንዲሁም በመንፈሳዊ እና በክርስቲያናዊ ተቋማት ውስጥ እየተቀጠሩ በኃላፊነት ማገልገል ጀምረዋል። ከዚህ የተነሳም ቤተ ክርስቲያንም ሆነች መሪዎቿ እና አገልጋዮቿ የሚሰደዱበት እና የሚገፉበት ዘመን አልፎ የሚከበሩበት እና በበጎ ተጽእኖአቸው የሚወደሱበት ዘመን እየመጣ ነበር።*

*በዚሁ ጊዜ በአስጨናቂው የስደት ዘመን እንደሚገባ የወንጌሉን ብርሃን ያበራችው ጌጃም በብዙ ፍሬ ተሞልታ ተጽእኖዋ የጨመረ፣ ልጆች ተወዳጅ መንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ ትምህርት የሚያገኙበት ትምህርት ቤት፣ አገልጋዮች ለአገልግሎት የሚዘጋጁባት ማዕከል፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች እና መሪዎች ለአጠቃላይ ወንጌላውያን አማኞች በረከት የሚሆኑ፣ ዘማሪያንን፣ ሰባኪያንን፣ የሥነ-ጽሑፍ ባለሙያዎችን ... ወዘተ እያፈራች ብርሃኗ ጨምሯል።*

*ይሁንና በዘመኑ ከነበረው የቤተ ክርስቲያን መብት መገደብ እና በከተማው የነበሩ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት በቁጥር እጅግ ጥቂት ከመሆናቸው የተነሳ ጌጃ የአንድ አካባቢን ሳይሆን የመላ አዲስ አበባን የቃለ ሕይወት አባላት የያዘች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። የጌጃ አባላት ከኮተቤ ሰሜን ጫፍ እስከ ደቡብ ምስራቁ ካራ ቆሬ ጫፍ፣ ከደቡብ አቃቂ እስከ ሰሜኑ አዲሱ ገበያ በብዙ ኪሎ ሜትር ርቀት ተበታትነው ይኖሩ ነበር። በየክፍለ ሃገሩ የሚያመልኩበት ቤተ ክርስቲያን ያልነበራቸው አማኞችም አዲስ አበባ ሲመጡ ጌጃ መጠጊያቸው ነበረች። ቤተ ክርስቲያኒቱ ብዙዎች ብዙ ኪሎ*

*ሜትሮች አቋርጠው የሚመጡባት እንደ ኢየሩሳሌም ያለች ቅድስት ምድር ሆና ትታይ ነበር።*

*በዚሁ ሁኔታ ዓመታት እየነጎዱ እያለም አንድ እሁድ ከሰዓት በኋላ አራት ኪሎ በሚገኘውና የቤተ ክርስቲያኒቱ የብዙ ዘመን አገልጋዮች በሆኑት ወ/ሮ ብርቱካን ጥላሁን እና አቶ ብርሃኑ መኖሪያ ቤት የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የመሪዎች እና የአገልጋዮች ኅብረት ይካሄድ ነበር። በዚሁ ዕለት ወንጌላዊ ኬዳሞም የኅብረቱ አካል ሆነው በስፍራው ተገኝተዋል። የኅብረቱ ፕሮግራም ከተጀመረ በኋላም ከእግዚአብሔር ቃል መልእክት እንዲያቀርቡ ተጋበዙ።*

*ወንጌላዊው በእለቱ መልእክት ለማቅረብ ተዘጋጅተው ባይሄዱም ባሉበት ሆነው ጸለዩ እና የሚያነቡት ቃል ተሰጣቸው። መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ከፍተውም ለጉባኤው ያንን ቃል አነበቡ። 2ኛ ነገስት 6፡1-7*

> *"የነቢያትም ልጆች ኤልሳዕን እነሆ በፊትህ የምንቀመጥበት ስፍራ ጠብቦናል። ወደ ዮርዳኖስም እንሂድ፣ ከእኛም እያንዳንዱ ከዚያ ምሰሶ ያምጣ የምንቀመጥበትንም ስፍራ በዚያ እንሥራ አሉት፤ እርሱም ሂዱ አለ። ..." ቁጥር 2*

*ክፍሉን ለጉባኤው ካነበቡ በኋላም "በጸሎት ላይ እያለሁ ነው ይህ ቃል የመጣልኝ። እኛም አሁን ያለንበት ጸሎት ቤት ጠብቦናል። ለወደፊት ምንድን ነው የምንሆነው? የቤቱ መጥበብም በጣም አስቸግሮናልና ዝም ብለን እንየው? የግድ አንድ እርምጃ መውሰድ አለብን።" ብለው ተናገሩ። "ጌጃ እንዲሁ ባለ ሁኔታ መቀጠል የለባትም " አሉ። ይህ ሃሳብ ከተነገረ በኋላ በስፍራው የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እና አገልጋዮች በሙሉ በአንድ ሃሳብ ተስማሙ።*

*በዕለቱ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የሆኑት አቶ ላቀው ተሰማ፣ አቶ ጥላሁን ኃይሌ፣ አቶ ወልደ አምላክ ዲኬ፣ አቶ ደምሴ ማዴ፣ አቶ ሽፈራው ወ/ሚካኤል፣ አቶ ብርሃኑ ደረሰ እና ባለቤቶቻቸው በሙሉ በስፍራው ነበሩ። ከወንጌላዊ ኬዳሞ ጋር አገልጋይ የነበሩትም ሽመልስ ወዳጆ፣ ወ/ሮ ቀለሟ ኃይሌ እና ሽፈራው ፈይሳም በስፍራው ነበሩ። ሁሉም እግዚአብሔር በዕለቱ ባስተላለፈላቸው ሃሳብ ተስማምተው በዚያ ስብሰባ ላይ ስለ ጉዳዩ ጸሎት ተደረገ።*

---------------------//---------------------

በዚያች የአገልጋዮች እና የመሪዎች ኅብረት ቀን ቤተ ክርስቲያን ቦታ ስለጠበባት እና አባላት ስለበዙ ተጨማሪ ጸሎት ቤት ለመሥራት ሲታሰብ በመጀመሪያ ያደረግነው መጸለይ ነበር። በጉዳዩ ላይ ከጸለይን በኋላም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቦታ እንፈልግ የሚል ሃሳብ በማምጣታቸው ለጸሎት ቤት መሥሪያ የሚሆን ቦታ መፈለግ ጀመርን። በመጀመሪያ አዲስ የአምልኮ ጣቢያ ሆኖ የሚወጣ አካባቢ ተብሎ የታሰበውም ቦሌ ነበር። ወደ ቦሌ አጥቢያ ለመትከል ታስቦ ቦታ ሲፈለግም አጥቢያዋ ለቦሌ ብቻ ሳይሆን

ለኮተቤ አካባቢ ነዋሪዎችም ጭምር እንድትሆን ታስቦ አማካይ ስፍራ ላይ ቦታ ለመያዝ ጥረት ተደርጎ ነበር። በተለይ ምስራቅ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከመተከሏ በፊት ቦታው ስላልተያዘ ጌጃ ልትከፍት ካቀደችው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር አብሮ እንዲሰጠን በዚያ ስፍራ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ለመንግስት አካላት ጥያቄ ቀረበ።

በኮተቤ አካባቢ ላሉት ምዕመናን እንዲሆንም ገደራ ሆቴል ያለበት አካባቢም ቦታ ለመያዝ ታስቦ ነበር። በዚሁ የተለያዩ ሃሳቦች መካከልም ጉዳዩ ለውሳኔ የሚያስቸግር ስለነበር ጸሎት በደንብ ይጸለይ ነበር። በተለይ በእነ አቶ በቀለ ቤት ሌሎች ብዙ ሰዎችም ተሰብስበን በዚህ ጉዳይ ላይ በጣም ጽኑ ጸሎት ስለጸለይን እግዚአብሔርም ሰማን።

በመጨረሻም የቦሌ ቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና የ2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚከፈትበት ቦታ ተገኝቶ ቦሌ ቃለ ሕይወት የመጀመሪያዋ የጌጃ አጥቢያ ሆና ወጣች። ከዚህ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተበረታትተው በልዩ ልዩ ቦታዎች አጥቢያ ለማውጣት የተጠናከረ እንቅስቃሴ ተጀመረ። የኛ አባላት በብዛት ባሉበት በመካኒሳ፣ በአስኮ፣ በኮተቤ እና በቀራኒዮ አካባቢዎች የተለያዩ አጥቢያዎች ተራ በተራ እንዲወጡም ሥራ ተጀመረ።

ይህንን እርምጃ በመውሰድ ቤተ ክርስቲያናትን በየስፍራው የመትከል እንቅስቃሴ ሲካሄድ አንዳንድ የጌጃን አጥቢያ እንደ ብቸኛ የእግዚአብሔር መገኛ የሚያዩ አባላት እና አገልጋይ መሪዎች ቅር ተሰኝተው ነበር። እነ ተስፋዬ ባህታ በጣም ተቃውመው የነበረ ሲሆን የወ/ሮ ሰብለ ወንድም የሆነው ጌዲዮን ወልደ ሰማያትም ይህን ሃሳብ በጣም ይቃወሙ እና "ልትበታትኑን ነው፤ ልታለያዩን ነው፣ ልታራርቁን ነው" እያሉ ይናገሩም ነበር።

በጊዜው እኔ እና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ ጉዳይ ቅር የተሰኙ ሰዎች ቤት እየሄድን ይህ የወንጌል አካሄድ ሁኔታ መሆኑን በመግለጽ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያንም ወንጌል ከኢየሩሳሌም ተነስቶ በይሁዳና በሰማሪያ ብሎም እስከ ምድር ዳርቻ መሄዱን በመንገር የማሳመን ሥራ እንሠራ ነበር።

በዚህ ቤተ ክርስቲያንን በተለያዩ ቦታዎች የመትከል ሃሳብ ዙሪያ እኔ በመጀመሪያ ራእዩን እንደተቀበልኩ ለሁሉም ብናገር እኔን ወንጌላዊ በመሆኔ እንደተቀጣሪ እና ሠራተኛ ስለሚያዩ ብቻ ሰዎች በጣም ሊቃወሙኝ ይችሉ ነበር። ነገር ግን እኔ ሃሳቡን በመጀመሪያ በወቅቱ ሽማግሌ ለነበረው ለአቶ ሽፈራው ወ/ሚካኤል በማቅረብ አሳመንኩት። እርሱም በአስፈላጊነቱ አምኖ እንቅስቃሴ ሲጀምር የሃሳቡ ተቃዋሚዎች እርሱን እና እኔን ቤተ ክርስቲያንን ለመበተን እንደተነሳን እና ክፉ መንፈስ እንዳለብን በመናገር ይቃወሙን ነበር። ነገር ግን አቶ ሽፈራው ብልህ የአስተዳደር ሰው ስለሆነ እና የነገሮችን አካሄድ ያውቅ ስለነበር ሁሉንም ተቃውሞ ጸጥ አሰኝቶ ቤተ ክርስቲያናት የመትከል አገልግሎቱ መስመር ይዞ ሊሄድ ችሏል።

በዚህ ጊዜ አንዳንድ መሪዎች ሃሳቡን በይፋ ሲቃወሙ አንዳንዶች ለዘብተኛ ሆነው ወዳሸነፈው ለመሄድ በማሰብ መሀል ሰፋሪ ነበሩ። እንደ አዱኛ በዳዳ እና ሽመልስ ወዳጆ ያሉት ደግሞ ጉዳዩን በደንብ ደግፈው ውጤታማ እንዲሆን ይጥሩ ነበር።

በእርግጥ በቤተ ክርስቲያን ተከላው ወቅት አንዳንድ ችግሮች ያጋጥሙን ነበር። ለምሳሌ የኮተቤውን አጥቢያ ልንተክል በተነሳን ጊዜ እኔ በዚያ ቤተ ክርስቲያን ከሚሆኑት የኮተቤ ሰዎች መሃል "ሽመልስ ወዳጆ እና ጌታቸው ወ/ገብርኤል ብቻ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራትም፣ ለማሳደግ እና ለማስተዳደር ይችላሉ የሚል እምነት ነበረኝ። ከእነርሱ በታች ያሉት ግን የተሻለ ጠቃሚ ሃሳብ ለማምጣት የሚችሉ ስላልሆኑ እነርሱን ማሳደግ አለብን" ብዬ ተናገርኩ።

ይህንን በግልጽ በመናገሬ አንዳንዶች "እኛስ?" ብለው በቅሬታ ተነስተው ነበር። እኔም በግልጽ "እናንተ በልዩ ልዩ አገልግሎት ለመተባበር ትችላላችሁ እንጂ ቤተ ክርስቲያንን አሁን ለመምራት አትችሉም፤ በልምድና በመንፈሳዊ እውቀት ማደግ አለባችሁ።" በማለቴ አንዳንዶቹ በጊዜው አዝነውብኝ ነበር። በወቅቱ በቁጣ ከተነሱብኝ መካከል አለማየሁ ጎሹ አንዱ ነበር። እርሱም በጣም ተበሳጭቶ በቁጣ ሲናገረኝ "እኔ ምንም ብትቆጣኝ ቤተ ክርስቲያንን የሚመራ ሃሳብ ለማምጣት አንተ ገና ስለሆንክ ማደግ አለብህ" አልኩት። ከዚያ በኋላም እንዳልኩት አለማየሁ በመንፈሳዊ እውቀት እና በልምድ አድጎ የኮተቤ ቃለ ሕይወት ካሏት በሳል መሪዎች አንዱ መሆን ችሏል።

ያኔ የኮተቤ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ራሷን የቻለች አጥቢያ ሆና ከጌጃ ስትወጣ ከ70 የማይበልጡ አባላት ብቻ ነበሯት። ለረጅም ዘመናትም የራሳቸው መሪዎች አስተዳደሩን ከመረከባቸው በፊት ከኛ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር ተስማምተን ራሴው ወደ ኮተቤ ሄጄ እያደርኩ አስተምራቸው ነበር። በዚያ ጊዜ በብዛት አስተምራቸው የነበረውም እነርሱን ሊያሳድጉ የሚችሉ በመንፈሳዊ ሕይወት ብቃትና በመንፈሳዊ እድገት ላይ ያተኮሩ ተከታታይ ትምህርቶችን ነበር። እግዚአብሔር ይመስገን፤ በመጨረሻ የኮተቤ መሪዎች አጥቢያይቱን ተረክበው መምራት ችለዋል።

የኮተቤ አጥቢያ የራሷን ቦታ ገዝታ ራሷን እንድታቋቁምም የጌጃዋ እናት ቤተ ክርስቲያን 90 ሺህ ብር ያህል ለግሳለች። አጥቢያይቱም ራሷን በራሷ ለመቻል እና ለማደግ ትጥር ነበር።

አንድ ቀን ኮተቤ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የእሁድ ስብከት ለማቅረብ ቮልስ ዋገን መኪናዬን እያንጣረርኩ በማለዳ እገሰግስ ነበር። የአስመራ መንገድን (የዛሬው ኃይሌ ገብረ ሥላሴ ጎዳና ማለት ነው) አቋርጬ እየሄድኩም ልክ መገናኛ አካባቢ ስደርስ እግዚአብሔር በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 3፡7-8 ላይ ያለውን ሃሳብ የተመረኮዘ የተለየ መልእክት ሰጠኝ።

> *"የዳዊት መክፈቻ ያለው የሚከፍት የሚዘጋም የሌለ፤ የሚዘጋ የሚከፍትም የሌለ፤ ቅዱስ እና እውነተኛ የሆነው እርሱ እንዲህ ይላል። ሥራህን አውቃለሁ፤ እነሆ፦ በአንተ ፊት የተከፈተ በር*

*ሰጥቼሃለሁ፤ ማንም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቃሃልና፡- ስሜንም አልካድክምና፡፡" ይላል፡፡*

እኔም "እግዚአብሔርን በኛ ማንነት አንወስነውም፡፡ እናንተ በሁሉም አቅጣጫ ደካሞች ብትሆኑም የዚህች ቤተ ክርስቲያን መክፈቻ ያለው በጌታ ኢየሱስ እጅ ነው፡፡ በቃሉ እንደተጻፈውም እርሱ የከፈተውን ማንም ሊዘጋው አይችልም፡፡" እያልኩ እግዚአብሔር የሰጠኝን መልእክት አቀረብኩ፡፡ ይህ መልእክት አስቀድሜ ጽፌ ያዘጋጀሁት አልነበረም፡፡ በድንገት በመንገድ ላይ ተቀበልኩት እንጂ፡፡ በቃ በዚያች ዕለት የሕዝቡ ልብ ተነክቶ በመነሳሳታቸው በዚያው ጉባዔ ላይ ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያ 26 ሺህ ብር ተሰበሰበ፡፡

ልክ እንደዚሁ እየዞርሁ በተለያዩ ቦታዎች ለሚከፈቱ አጥቢያዎች ሕዝቡን አገለግል እና ለሥራ አነሳሳ ነበር፡፡ ቀራኒዮ ያለችው አጥቢያ ስትጀመርም በመጀመሪያ የሰው ቤት ተከራይተን አገልግሎት መስጠት ተጀምሮ ያንን ቤት ቤተ ክርስቲያን እንዲመስል ያበጃጁ ነበር፡፡ አንድ ቀን ለመስበክ ወደ እዚያው በሄድኩ ጊዜ በመጀመሪያ "በዚህ ቤት እየተገለገላችሁ መኖር የምትፈልጉ እጃችሁን አውጡ" ብዬ ጠየቅሁ፤ ጥቂቶች አነሱ፡፡ ከዚያም "ከዚህ ወደ ተሻለና የራሳችሁ ወደ ሆነ ስፍራ መሄድ የምትፈልጉ" ብዬ ስጠይቅ ደግሞ ብዙዎች እጃቸውን አነሱ፡፡ "ያላችሁ አማራጭ እዚህ ቦታ ተጨናንቆ መኖር ወይም ወደ ሌላ የተሻለ ቦታ መሄድ ነው፡፡ ወደ ሌላ ቦታ ማን ሊሄድ ይችላል? ወደ ሌላ ቦታ ሊሄድ የሚችለው ራሱን እና ገንዘቡን ለጌታ የሰጠ ሰው ነው፡፡" በማለት በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8 ላይ ባለው ሃሳብ ላይ የተመሠረተ ስብከት ሰበክሁ፡፡

ስብከቴን ሳጠቃልልም ጥቂት ገንዘብ ከኪሴ አውጥቼ ሰጠሁ እና ሌሎችም እንዲሰጡ እድል ሰጠሁ፡፡ ብሩም ከየሰዉ ኪስ እና ቦርሳ ጎረፈና ከፍተኛ ገንዘብ ተሰበሰበ፡፡ ዛሬ ያቺ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ቦታ ላይ በወይራ ሰፈር የአምልኮ ሕንጻ ገንብታለች፡፡ ከእርሷ የወጣችው የካራ ቆሬ አጥቢያ ቃለ ሕይወትም እንዲሁ በሁሉ አቅጣጫ ራሷን የቻለች ሆናለች፡፡ እኔም ወደ ካራቆሬ አጥቢያም በተደጋጋሚ ሄጄ አገለግያቸዋለሁ፡፡ ሁል ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የሚሠራው የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን፡፡

በሁለተኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8 ውስጥ ባለው ሃሳብ ላይ ተመርኩዤ ያዘጋጀሁት ስብከት "ለታላቁ የፍቅር ስጦታ መስጠት" የሚል ርዕስ የነበረው ሲሆን በመጀመሪያ አዘጋጅቼ የሰበክሁት በቦሌ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነበር፡፡ ከዚያ በኋላም በብዙ ቦታዎች የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት የእግዚአብሔር ሕዝብ በልግስና እንዲሰጥ መልእክት ሆኗል፡፡

የመካኒሳ አጥቢያ መቋቋም ስትጀምርም እንዲሁ የአንድ ግለሰብ ቤት በመከራየት ነበር፡፡ አንድ ቀን በአቶ ሽፈራው ወ/ሚካኤል ቤት ሰባት የሚሆኑ የመካኒሳ አካባቢ ነዋሪ የጌዳ ሽማግሌዎች እና እኔ ለጸሎት ተሰብስበናል፡፡ በጊዜው የምንጸልይበት ርእስም በዚያ አካባቢ የራሳችንን የአምልኮ ሕንፃ ስለመሥራት ነበር፡፡

በዕለቱ በጉዳዩ ላይ በኃይል ድምጻችንን ከፍ አድርገን እንጸልይ ነበር። እኔ በልቤ እግዚአብሔርን "በዚህ አካባቢ ጸሎት ቤት ለመገንባት ምን ያህል ብር ያስፈልገናል?" ብዬ ጠየቅሁት። መንፈስ ቅዱስም "ስድስት መቶ ሺህ ብር ነው፤ ይህንን ገንዘብም አሁን ያሉት አባላት ሊሰጡ ይችላሉ" አለኝ።

ወዲያው ከጸሎቱ ስንነሳ "እግዚአብሔር እንዲህ ብሎኛል" ብዬ ጌታ ለልቤ የተናረኝን ስነግራቸው "በቃ መስጠቱን ዛሬ እኛ እንጀምር።" በማለት በዕለቱ በስፍራው ከነበርነው ጥቂት ሰዎች አንድ ሺህ ስምንት መቶ ብር ተሰብስቦ ወዲያው ወደ ሥራ ተገባ። የጊጃ አጥቢያም ሦስት መቶ ስድሳ ሺህ ብር ለቦታ መግዣ በመለገሷ ቦታው ከሣር ቤቶች አካባቢ ትንሽ ገባ ብሎ ተገዛ። ይህ ከመሆኑ በፊት በነበረ አንድ ዕለት የአዲስ ተተካይዋ አጥቢያ አባላትንም በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ሰብስበን የመካኒሳን አጥቢያ መሥራት እንችላለን አንችልም በሚል ርእስ ውይይት አካሂደን ነበር። በጊዜው አባላቱ በሙሉ በአንድ ድምጽ እንችላለን ብለን ነበር። እግዚአብሔርም እንደ እምነታችን አደረገልን።

ከዚህ በኋላ በአጥቢያይቱ ጸሎት ቤት ፕሮግራም አካሂደን በዚያ ፕሮግራም ላይ 73 ሺህ ብር ተሰጠ። በአዲሱ ቦታ ላይም የሕንፃ ግንባታ ለመጀመር የመሠረት ድንጋይ የሚጣልበት በዓል ሲካሄድ እኔ መልእክት አቀረብኩ። በዚያ ዕለትም ከተገኘው ሕዝብ 126 ሺህ ብር ተሰበሰበ።

በመካኒሳ የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ቤት ግንባታ ሥራ ውስጥ ሕዝቡ በሙሉ በመጀመሪያ ቃል እንደገባው በሙሉ ልቡ ነበር የተረባረበው። በተለይ የዚያች አጥቢያ ሽማግሌ የነበረው (የሽማግሌዎች ሰብሳቢም ሆኖ ለብዙ ጊዜ አገልግሏል) አቶ ዘለቀ ገለቱ ለቤቱ ቶሎ መጠናቀቅ በጣም የላቀ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ይህ ወንድም ያኔ ጊዜውን፣ ጉልበቱንና ገንዘቡን መስዋዕት አድርጎ ሰጥቶ ነበር። ከዚህ የተነሳም አጥቢያይቱ የተዋበ የአምልኮ ሕንፃ ሠርታ ለማጠናቀቅ ችላለች።

በዚያ ዘመን ጊጃ ቃለ ሕይወት በማስተማር እና አባላትን በማደራጀት ብቻ ሳይሆን የሚተከሉ አጥቢያዎች ራሳቸውን እንዲችሉ ለቦታ መግዣ የሚሆን ገንዘብ በመስጠት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ታደርግ ነበር። የአስኮ አጥቢያ ስትተከልም እንዲሁ ለቦታ መግዣ የሚሆን ገንዘብ በመስጠቷ የአስኮ ቃለ ሕይወት ዛሬ የተዋበ የአምልኮ ሕንፃ በስፍራው ላይ ገንብታለች።

በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ልክ በ2ኛ ነገስት የነቢያት ልጆች ስፍራ ጠብቦናል ብለው ተነስተው እንደነበረው ሁሉ እኛንም አስነስቶን በአዲስ አበባ ከተማ አንድ የነበረችው ጸሎት ቤት በጥቂት ዓመታት ውስጥ ተስፋፍታ ከ10 በላይ እንድትሆን አደረገ። እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ነው።

# ምዕራፍ ፳፮

# በኢየሱስ ዱካዎች ላይ መራመድ

## የእስራኤል ጉዞዬ

*በጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሲካሄዱ ከነበሩ መልካም አገልግሎቶች መካከል አንዱ የመዘምራን አገልግሎት ነበር። በጊዜው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሳይቀሩ በዘማሪነት እያገለገሉ ቆይተው ስፍራውን ለወጣቶች ለቅቀዋል። አስከፊው የደርግ ዘመን ሲመጣም የጌጃ "ሀ" መዘምራን ቡድን ለብዙዎች መጽናኛ የሚሆን ዝማሬን የሚያሰማ፣ ብዙዎች በእምነት እንዲጠነክሩ ያገለገለና በዚያ ዘመን በአገሪቱ ከነበሩ ጠንካራ የመዘምራን ቡድኖች አንዱ መሆን የቻለ ነበር።*

*በዚህ የመዘምራን ቡድን ውስጥ አባል የነበሩ ወጣቶች በቡድኑ ውስጥ ባለው ጠንካራ ኅብረት እየታገዙ በጽናት ማገልገል እና ራሳቸውንም በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊው ሕይወት ማሳደግ ችለዋል።*

*በእርግጥ በዚህ ቡድን ውስጥ የነበሩና በሂደት ከዚህ ጠንካራ መንፈሳዊ አቋም የተለዩም ነበሩ። በደርግ ዘመን ጅማሬ ላይ አንድ ዕለት በጌጃ መድረክ ላይ ይኸው የመዘምራን ቡድን አገልግሎ ከመድረክ ወረደ። ወንጌላዊ ኬዳሞም የእሁዱ መልእክት አቅራቢ ስለነበሩ አገልግለው ከመድረኩ እንደ ወረዱ የመዘምራን ቡድኑ የሁለተኛ ክፌለ ጊዜ ዝማሬውን አቀረበ።*

*የዕለቱ ፐሮግራም ከተጠናቀቀ በኋላም ወንጌላዊው በመዘምራኑ የዝማሬ አገልግሎት ወቅት የታዘቡትን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተናገሩ። "ከእነዚህ መዘምራን መካከል ያላመኑ ልጆች አሉ። ልጆቹ በደንብ ተምረው ጌታን አውቀው ማገልገል አለባቸው" አሉ።*

*ወንጌላዊው እንደተናገሩትም በጊዜው በመዘምራን ቡድኑ ውስጥ ከነበሩት መካከል ሁለት ወጣቶች (አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት) ብዙም ሳይቆዩ ለእድገት በኅብረት ዘመቻ በሄዱበት ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው ቀሩ። ሴቲቱም እንዲሁ ክርስትናውን*

ከቤተሰብ ያገኘችው እንጂ በግሏ የያዘችው ስላልነበር ወደ ኋላ አፈገፈገች። እነዚህ ወጣቶች እግዚአብሔር የለም ባዩን ፓርቲ ተቀላቅለውም ከሕይወት ጎድለዋል።

ከቆይታ በኋላ ግን ወንጌላዊ ኬዳሞ ለአጠቃላይ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አባላት እንደሚያደርጉት ሁሉ መዘምራኑንም እየተከታተሉ በማስተማር ጠንካራ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖራቸው ማገዛቸውን ቀጠሉ። እግዚአብሔርም በብዙ አቅጣጫ አሳድጓቸው ከመዘምራን ቡድኑ ባሻገር በርካታ የግል የዝማሬ አገልጋዮችን ጌጃ ቃለ ሕይወት ማፍራት ችላለች።

በ1974 ዓ.ም ኬዳሞ ከዚሁ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የ"ሀ" መዘምራን ጋር የትምህርት እና የኅብረት ጊዜ ለማሳለፍ ሶዶሬ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ተገኝተዋል። በዚሁ ከእሮብ እስከ ቅዳሜ ለመቆየት ተወስኖ በተሄደበት ጉዞ አገልጋዩ ለፋ ያለ የምክርና የትምህርት ጊዜ በማዘጋጀት ከመዘምራኑ ጋር ሲያሳልፉ ቆዩ። እግረ መንገዳቸውንም ከጠዋት እስከ ማታ ለአገልግሎት በመሮጥ የዛለ ሰውነታቸውን በሶደሬው ፍል ውሃ በማራስ ተዝናኑ። እሮብ እና ሐሙስ በውቡ የሶዶሬ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል የመዝናኛ ስፍራ ለመዘምራን ቡድን መልካም የእረፍት እና የመማሪያ ቀን ሆኖ አለፈ። ኬዳሞም ከአዲስ አበባ ቀዝቃዛ አየር፣ ከአገልግሎት፣ እና ከልዩ ልዩ ኃላፊነት ጫና ዞር ብለው የመዘምራን ቡድኑ አባል ከሆነችው ልጃቸው ሣራ በስተቀር ከተቀረው ቤተሰባቸው ተለይተው በጥቂት አስርት ከሚቆጠሩት ዘማርያን ጋር የአባት እና የልጅ ምክክር እና የትምህርት ጊዜ ሲያሳልፉ ቆዩ።

ዓርብ ማለዳ ኬዳሞ እንደ ልማዳቸው ሶደሬ የሚገኝበት ስምጥ ሸለቆ አእዋፍ ሳይንጫጩ በማለዳ ተነስተው እግዚአብሔርን ያመሰግኑ እና በጸሎት ይተጉ ጀመር። በድንገትም መንፈስ ቅዱስ ያላሰቡትን እንግዳ መልእክት ነገራቸው። በግልጽ ቋንቋ "አንተ እስራኤልን ሄደህ ታያለህ!" አላቸው። ነገሩ ያላሰቡት እንግዳ ነገር ስለሆነባቸውም "እንዴት? " ብለው ጠየቁ። ያው በተመስጦ ራእይ ውስጥ የመጣ ድምጽም በድጋሚ አስቀድሞ የተናገራቸውን አረጋገጠላቸው። ወንጌላዊውም በዚያ ማለዳ የጸሎት ሰዓታቸው በመጣው የራእይ መልእክት እየተደነቁ ነቁ። ወዲያውም ተሰብስበው ወደ ነበሩት ዘማርያን ሄደው እግዚአብሔር የተናገራቸውን አበሰሩ። "ዛሬ ማለዳ እግዚአብሔር ;እስራኤል ትሄዳለህ; ብሎኛል። እናንተም ለምስክርነት እንዲሆን ይህንኑ ስሙ። እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ ነው ይህን የተናገረውን ቃል ይፈጽማል" አሉአቸው።

የጌጃ "ሀ " መዘምራን ቡድንም የዚህን የተስፋ ቃል ፍጻሜ ለመጠባበቅ እና የእግዚአብሔርን ታማኝነት ለመመስከር መልዕክቱን በልባቸው በማኖር የሶደሬውን ቆይታ አጠናቅቀውም ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። ይህ የተስፋ ቃል ከተነገረ በኋላም ዓመታት ነጎዱ። ለኬዳሞ በራእይ የተነገረው ቃልም ስለመሄዳቸው እንጂ ከእርሳቸው ሊደረግ የሚገባው አንዳችም መመሪያ አልነበረውምና ወንጌላዊው እንደ ቀድሞው ሁሉ በጌጃ ቃለ ሕይወት አገልግሎት ተጠምደው ይባትሉ ገቡ። ነገሩ ከተነገረ ከአምስት ዓመታት በላይ አለፉ።

*በድንገት ግን በአስገራሚ ሁኔታ ውስጥ አልፎ የተነገረው የተስፋ ቃል እውን ሆነ። ኬዳምም ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በሄደባቸው መንገዶች እና በእግሩ ዱካዎች እየተረማመዱ፤ አሻግረው ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የሆነውን እያሰቡ በምናብ ሳይሆን በአካል ተጓዙ። ጌታ ኢየሱስ መስቀል ተሸክሞ እየተንገላታ የወጣውን የቀራኒዮ ዳገትም በርሳቸውን ይዘው እያለቀሱ ወጡ። "አንተን እየገረፉ ወሰዱህ ... ለኔ ነው መስቀል ተሸክመህ ይህን ዳገት የወጣኸው ...." እያሉ የክርስቶስን መከራ እያስታወሱ አነቡ። ልክ ዘማሪው እንዳለው፡-*

*"ለኔ ነው ያ መንከራተትህ፣*

*ለኔ ነው የደም ላብ ያላበህ፣*

*ለኔ ነው ህመሚ ያመመህ፣*

*ለኔ ነው ... ለኔ ነው"*

*(ዮሴፍ በቀለ)*

---------------------//--------------------

የእስራኤል ጉዞዬ አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ የተነገረኝ ቢሆንም ነገሩ ግን ቆይቶ ካልታሰበ አቅጣጫ መጣ። በድንገትም የኤስ አይ ኤም ሚሲዮናውያን የሆኑት እነ ፖሊ ቢልስኪ እኔ እና አቶ ሙላቱ ታዬ ወደ እስራኤል እንድንሄድ ለቃለ ሕይወት ጥያቄ አቀረቡ። የጥያቄው መነሻም በጌጃ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በማስተማር ይረዳን የነበረው ሚ/ር ስቲቭ ስትራውስ ነበር። እርሱ አገሩ ሄዶ ሳለ እኔ ወደ እስራኤል እንድሄድ ከቤተሰቦቹ እና ከቤተ ክርስቲያናቸው ጋር ተማከረ። በኋላም ለማስተርጎምም እንዲረዳ አቶ ሙላቱ ታዬ አብሮኝ እንዲሄድ ወሰኑ።

እንደነገርኳችሁም የኤስ አይ ኤም ወገኖቻችን ጥያቄውን ለእነ አቶ ጥላሁን ኃይሌ በማቅረባቸው እነ አቶ ጥላሁንም ነገሩን ለእኔ ሳያሳውቁ ፈቃደኝነታቸውን በመግለጽ ጉዞውን ለማመቻቸት እንቅስቃሴ ተጀመረ። ለኔም ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ነበር የተነገረኝ። ሚ/ር ስቲቭ ስትራውስም መጥቶ ለጉዞ የሚያስፈልገኝን የፓስፖርት እና የይለፍ ፈቃድ ማውጣት እንዳስፈጽም እርሱ ደግሞ ያን ጊዜ ወደ እስራኤል የሚሄደው በግብጽ በኩል ስለነበር በግብጽ ኤምባሲ በኩል የሚያስፈልገውን እንደሚያስፈጽም ነገረኝ። እኔም በተሰጠኝ መመሪያ መሠረት ከኢትዮጵያ መንግስት ማግኘት የሚገባኝን ህጋዊ የጉዞ ሰነድ በሙሉ አስፈጽሜ ብዘጋጅም እርሱ ወደ ግብጽ ኤምባሲ ሄዶ ሲጠይቅ ያጋጠመው የኤምባሲ ሰው እንግሊዝኛ በደንብ የማይችል ስለነበር ሳይግባቡ ቀርተዋል። ስቲቭ በእንግሊዘኛ ያኛው በአረብኛ እያወሩ አንዱ ሌላው ሳይረዳ ቀርተው ሰውየው ;ከወር በፊት ማለቅ አለበት ሲል;፣ ስቲቭ ;ከወር በኋላ ና; ያለው መስሎት ወደ መጣበት ተመልሶ አንድ ወር ቆይቶ ወደ ግብጽ ኤምባሲ ሲሄድ ጊዜው በማለፉ ምንም ሊረዱት አልቻሉም። ስለሆነም ለኔ የግብጽ ቪዛ ብቻ ተሰጥቶኝ ወደ እስራኤል የመግቢያ ቪዛ ሳይመታልኝ ቀረ። ስቲቭም ስለዚህ ሁኔታ ሳይነግረኝ

ዝም አለ። እኔም ምንም ሳላውቅ ለመሄድ ተዘጋጅቼ ወደ እስራኤል የሚወስደኝ ትኬት አስቀርጬ በጉዞ ዙሪያ ስጸልይ ከረምኩ።

የጉዞው ቀን ሲቃረብም አቶ ሙላቱ ታዬ መሄድ ስላልቻለ የደብረ ብርሃን ልጅ የሆነው ይቅናሸዋ ከኔ ጋር እንዲሄድ ተወሰነ። በመጨረሻም ከይቅናሸዋ ጋር ተያይዘን ለመጓዝ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ አመራንና ወደ መንገደኞች መግቢያ ደርሰን ፓስፖርታችንን እና ትኬታችንን ለደህንነት ተቆጣጣሪ ሰጠን። ተቆጣጣሪውም "የእናንተ ትኬት የተቆረጠው እስከ እስራኤል ቢሆንም ቪዛችሁ ግን እስከ ግብጽ ድረስ ብቻ ነው።" ብሎ አፋጠጠን።

በዚህ ጊዜ እኔ አብሮኝ የሚሄደው ይቅናሸዋንም ትቼ ወደ አንድ ለጸሎት ምቹ የሆነ ሰወር ያለ ቦታ ሄድኩ እና ተንበርክኬ መጸለይ ጀመርኩ። ለጸሎት ከተንበረከኩበት ሳልነሳም ከእግዚአብሔር መንፈስ መልእክት ተቀበልኩ። "እስራኤል በግብጽ አልቀረም፤ አንተም ከግብጽ አትመለስም፤ እስራኤልን ታያለህ።" የሚል ነበር መልእክቱ።

ወዲያውም በድንጋጤ ውስጥ ሆኛ ወደ ቆመው ይቅናሸዋ ተጠግቼ "ይቅናሸዋ እግዚአብሔር 'ትሄዳለህ' ብሎ ተናግሮኛል። እንሄዳለን እዚሁ አንቀርም።" ስለው እርሱም "አምን እንሄዳለን እግዚአብሔር ያደርጋል።" አለኝ። እኛ እየተነጋገርን እያለንም ጉዳያችን ግራ አጋብቶት ፓስፖርታችንን የያዘው የደህንነት ተቆጣጣሪ ፓስፖርታችንን ይዞ ከሄደበት ተመልሶ ወደ እኛ በመምጣት ሌላ ጊዜ ፈጽሞ ሊባል የማይችል አስገራሚ ነገር ነገረን። "ፓስፖርታችሁ እና ትኬታችሁ የተለያየ ነገር ነው የያዘው። በራሳችሁ ፈቃድ ፈርማችሁ መሄድ ከፈለጋችሁ ፈርማችሁ መሄድ ትችላላችሁ።" አለን። እኛም ግጥም አድርገን ፈርመን አለፍን እና ተፈትሸን አውሮፕላን ተሳፈርን። አውሮፕላኑም እኛን ይዞ ወደ ግብጽ በረረ።

ግብጽ እንደደረስንም የእስራኤል ድንበር ወደሚገኝበት የርዳኖስ በመሻገር ከጋበዙን ከአሜሪካ የመጡ የስቲቭ ስትራውስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ጋር ተገናኘን። እሁድ ማታ እዚያ ገብተን ካደርን በኂላም ሰኞ እና ማክሰኞ የዮርዳኖስን ምድረ በዳ ስንጎበኝ ዋልን። በዚሁ ጊዜም እስራኤላውያን ለ40 ዓመታት የተንከራተቱበትን የሲና በረሃ፣ ከዓለቱ ውሃ የፈለቀበትን፣ አሮን የተቀበረበትን ስፍራ ሁሉ እየዞርን ጎበኘን።

ከዚያም በጣም አስደናቂ የሆነውን የኤሳው ዘሮች ኤዶማውያን የነበሩበትን የኤዶም ሸለቆን ጎበኘን። ይህንን አስገራሚ ታላቅ ሸለቆ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ገብተን ያየነው ቢሆንም በግራና በቀኝ ያለው ተራራ

ጋርዶት የፀሐይ ብርሃን ስለማያገኝ ጨለም ያለ ነበር። በዚህ ሸለቆ ውስጥ እያለንም በሚስተር ስቲቭ ስትራውስ አባት አስተማሪነት የአብድዩን መጽሐፍ አጠናን።

በእውነት በዚያ ስፍራ ያየነው እና በአብድዩ መጽሐፍ ተጽፎ ያጠናነው ነገር ፍጹም ተመሳሳይ እና አንዱ የሌላው ትክክለኛ ግልባጭ ሆኖ ነበር ያገኘነው። በቦታው

ኤዶማውያን አምልኮ ያደርጉበት የነበረው ስፍራ እና እንደ ግድግዳ ቀጥ ያለ መልክዓ ምድር አለ። በዚያ ዘመን ኤዶማውያን በአራት ነገር ይመኩ ነበር። አንደኛ ያለንበት ቦታ ተራራማና መግቢያውም አንድ ብቻ ስለሆነ ማንም ገብቶ ሊያገኘን አይችልም ይሉ ነበር። ሁለተኛ በኤዶም ጠቢባን የሆኑ ዓይኖች ነበሩ። ሦስተኛ አገሩ ኃያል ስለነበር እንደዛሬዋ አሜሪካ ተሰሚነት ነበረው። አራተኛ ኤዶማውያን ራሣቸው ኃያላን ጦረኞች ነበሩ።

እግዚአብሔር ግን በቃሉ "ከተራራ ላይ እወረውርሃለሁ፤ ጠቢባንን መኃይም አደርጋለሁ፤ እውቀትህን እወስዳለሁ፣ ተሰሚነት እና ሞገስህንም ካንተ እወስዳለሁ፣ ኃያላን ጦረኞችህም ይፈራሉ።" ብሎ ነበር። ይህም እውን ሆኖ ልክ አብድዩ እንደተነበየው ቦታው ላይ ሰው የሚባል ጠፍቶ የወፍ ማደሪያ ብቻ ሆኗል። እኔም ይህንን ሳይ አሽዋው ላይ ተንበርክኬ በታላቅ መደነቅ "እግዚአብሔር ሆይ እግዚአ ... ላንተ እና ለቃልህ!" አልኩ።

ይህን ሁሉ ካየን በኋላ ማክሰኞ ዕለት ቀን ላይ በጠረፍ በኩል ለመግባት ከዮርዳኖስ በአውቶብስ ወደ እስራኤል ሄድን። ከአሜሪካ የመጡ በሙሉ ወደ እስራኤል የመግቢያ ፈቃድ የያዙ ሲሆን እኛም ከእነርሱ ጋር ተቀላቅለን ወደ ስፍራው ደረስን። ድንበሩ ጋ ደርሰን ከአውቶብሱ እየወረድን እያለም እኔ በውስጤ "የእስራኤልን ምድር በኢየሱስ ስም እረግጣለሁ።" እያልኩ ነበር። ምክንያቱም ወደ እስራኤል የሚያስገባ ቪዛ እንደሌለኝ አውቅ ስለነበር የእግዚአብሔርን ተዓምር መጠባበቅ ስለነበረብኝ ነው።

በዚህ ሁኔታ ከመኪና ወርደን ተሰልፈን ወደ ፍተሻው ቦታ ተቃረብን። አቶ ደፋር የሚባሉ የቤተ ክርስቲያናችን አባል "እስራኤላውያንን ሰላም ስትል 'ሻሎም!' በል" ብለው በመከሩኝ መሠረት ገና ወደ እነርሱ እንደገባሁ ድምጼን ከፍ አድርጌ "ሻሎም!" አልኩ። በስፍራው ለጥበቃ የተሰለፈው ሁሉም ከዳር እስከ ዳር "ሻሎም!" በማለት መለሰልኝ። ከዚያም ተንበርክኬ የእስራኤልን ምድር እስም ጀመር። በጊዜው እኔ የማደርገውን ሁሉ እስከማላውቅ ድረስ በደስታ ያገኘሁትን ሁሉ ሳቅፍ የኔ ዕቃ ሳይፈተሽ እኔም ሳልጠየቅ ያለ ቪዛ ወደ እስራኤል ምድር ዘው ብዬ በመግባቴ አዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ እያለሁ እግዚአብሔር የተናገረኝ የተስፋ ቃል ተፈጸመ።

ወደ እስራኤል ምድር ዘልቀን ከገባን በኋላም አብረናቸው ከነበርነው አሜሪካውያን ጋር በመሆን ለአስራ አምስት ቀናት ያህል የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች የተፈጸሙባቸውን ታሪካዊ ስፍራዎች እየዞርን ጎበኘን። በእግዚአብሔር ቃል እንደተጻፈውም እኛ እንድንድን አሁን ለእስራኤላውያን የደህንነት መንገዱ ዝግ ነው። የሚያስጎበኘን እስራኤላዊ ራሱ ታሪኩን አሳምሮ እየነገረን እርሱ ግን አያምንበትም ነበር። እኔ በጉብኝታችን መጨረሻ ላይ ይህንኑ ለማረጋገጥም ሲያስጎበኘን የቆየውን እስራኤላዊ "አሁን ለእኛ የምትነግረውን ታምናለህ?" አልኩት። እርሱም "አላምንም" አለ። "እምነትህ ምንድን ነው?" ስለው ካቶሊክ ነኝ አለ። "ታዲያ ካቶሊክ ምን ልዩነት አለው?" ብዬ ስጠይቀው "በቃ እኔ ሥራ ስለሆነ እሠራለሁ እንጂ በዚህ ነገር ምንም

አላምንም።" ብሎ ስለ መለሰልኝ ለእነርሱ እንዴት በሩ ዝግ እንደሆነ በተጨባጭ ተረዳሁ።

በእስራኤል ምድር ጉብኝታችን ወቅት እንደገና ጌታ ኢየሱስ ከምድር ወደ አብ ከመሄዱ በፊት ለአሥራ አንዱ ሐዋርያት ስልጣን የሰጠበት እና የተሰናበተበት ቦታ ላይ ሆነን የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28ን አነበብን። እኔም ይህ ትእዛዝ ተፈጽሞ ወንጌል ከአስራ አንዱ ተነስቶ በአራቱም ማዕዘን ተሰብኮ በብዙ ትውልድ መካከል ተላልፎ ሄዶ ሄዶ እኔ ያለሁበት ሻሾጎ ድረስ ዘልቆ እኛ ቤት ደጃፍ ደርሶ እኔን ማግኘቱን አስቤ በጣም በመደነቁ እዚያው ያለሁበት ቦታ ተንበርክኬ በደስታ እያነባሁ ጌታን አመሰገንኩት።

ከዚህ በተጨማሪ ኢየሱስ የተወለደበትን የቤተልሔም የከብቶች በረት፣ የሞተበትን ቀራኒዮን እና የጎልጎታን ዳገት የተቀበረበትን መቃብር አይተናል። እኔም እርሱ የተቀበረበት መቃብር ውስጥ ገብቼ መቃብሩ ላይ ተጋደምኩ። በዚያ ስፍራም ሁሉን ስንጨርስ አብረናቸው ከነበርነው ነጮች ጋር የጌታ እራት ተቀበልን። እኔም ጌታ መስቀል ተሸክሞ የሄደበትን መንገድ እያለቀስኩ፤ "ለእኔ ነው መስቀል ተሸክመህ የወጣኸው፤ ለኔ ነው እየገረፉ የወሰዱህ፤ ለኔ ነው ይህን መራር መከራ የተቀበልከው።" እያልኩ ነበር የሄድኩት።

በዚያ ስፍራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አማኞችን እና ካህናቱን አግኝተን ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው ሄደን ጎብኝተናል። እኔም የእኛን ማንነትና እኔ ጌታን ከማመኔ በፊት ኦርቶዶክስ እንደነበርኩ ነግሬአቸው በደስታ ተቀብለውን ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ ትክክለኛ አምልኮ ብዙ ተወያየን። እኔም "እምነት በኢየሱስ ብቻ እንደሆነና ሌላ ሌላው ነገር ባይኖር ኦርቶዶክስ እና ፕሮቴስታንት አንድ መሆን እንደምንችል ነገርኳቸው። እነርሱም ነገሩ የእምነት አቋም ጉዳይ እንደሆነ እና ‹‹በአንድ ጥያቄ ብቻ የሚፈታ አይደለም።" ሲሉ መልሰውልኝ ተሰነባብተን ተለያየን።

ከእነርሱ ሌላም ጌታን የሚያምኑ አይሁዶች ስለነበሩ እነርሱ በልዩ ልዩ ሆቴሎች ፕሮግራም ይዘው እየተሰበሰቡ ከእኛ ጋር ቃል ተካፍለዋል። እኔም ዕድል እየተሰጠኝ ስለ እኛ አገር የወንጌል ሁኔታ መስክሬአለሁ።

በእስራኤል ምድር ሕዝቡ በጣም ኩራተኛ እንደሆነና እስራኤላውያን ትዕቢተኞች ናቸው ሲባል ብንሰማም እኔ ግን በጣም ትሁታን ሆነው ነው ያገኘኋቸው። እኛ በጎበኘናቸው ስፍራዎች ሁሉ አንድ ሥራ ይዞ ያለን ሰው ሄደን አንድ ነገር ብንጠይቀው ሥራውን አቁሞ እኛ የፈለግነውን ነገር ሄዶ ያመጣልን ነበር። በመኪና መንገድ ላይ ሁሉም ሕጉን ተከትሎ አንዱ ለሌላው ቅድሚያ እየሰጠ ፍጹም ሥርዓት አክብረው ነበር የሚንቀሳቀሱት።

የእስራኤላውያን ሌላው አስገራሚ ነገር ሰው ሁሉ መንገድ ላይ እየተርመሰመሰ ቆይቶ ልክ ዓርብ 12 ሰዓት ሲሞላ ሁሉ ነገር ባለበት ይቆማል። መኪና እየነዳ 12 ሰዓት የደረሰበት "ወደ ቤቱ ሳልገባ" ሳይል እዚያ መንገድ ዳር አቁሞ ይሄዳል። እስበለዚያ

ይቀጣል። ነገሩ ሁሉ ዓርብ 12 ሰዓት ቀጥ ብሎ እስከ ቅዳሜ 12 ሰዓት ይቆይና ልክ ሰንበቱ ሲያበቃ ወደ ቀድሞ ሁኔታው ይመለሳል። እግዚአብሔርን ስለሚፈሩ ሰንበትን በጣም ያከብራሉ።

እኔ እስራኤል አገር በነበረኝ ቆይታ ከመንፈሳዊው ነገር ባሻገርም የዮርዳኖስ ወንዝ መነሻ በሆነው አካባቢ ተገድቦ በተሠራ የመዋኛ ገንዳ ውስጥ ዋኝተናል። የዮርዳኖስ ወንዝ መጨረሻ የሚገባበት የጨው ባህር ድረስ ወርደንም ባህሩ ውስጥ ገብተን ዋኝተናል። የጨው ባህር የማያሰጥም አስገራሚ ባህር ሲሆን በውስጡ ምንም ሕይወት የሌለበት ጨዋማ ውሃ አለው። እኛም ጨዉ ሰውነታችንን እያቃጠለን ነበር የዋኘነው። የዮርዳኖስ ወንዝም ንጹሕ ውሃ ሆኖ ይመጣ እና ጨው ባህር ውስጥ ገብቶ ይጠፋል። በዚህ ስፍራ በነበረን ቆይታም ከባህሩ ጋር በተያያዘ መንፈሳዊ ነገር ተምረን ነበር። በትምህርታችንም ልክ እንደ ጨው ባህር ሁሉ የምንማራቸው ንጹሕ መንፈሳዊ ትምህርቶች ወደ እኛ ሕይወት ገብተው ሊጠፉ እና ሙት ሆነው ሊቀሩ እንደሚችሉ ነበር የተረዳነው።

እግዚአብሔር በ1974 ዓ.ም ቃል እንደገባልኝ እስራኤልን በአስደናቂ ሁኔታ ያለ ቪዛ ገብቼ እንድጎበኝ አደረገኝ። እኔን ምስኪኑን ገበሬ አንስቶ በኢሳይያስ 11 ላይ እንደተነገረውና "የማስተዋል የጥበብ .. መንፈስ ያርፍበታል" እንደተባለው ይህ ጥበብ በኔ ላይ አርፎ እጅግ ብዙ ሥራን ሠርቶ እኔን የታላላቅ ዶክተሮች እና ፕሮፌሰሮች አስተማሪ አድርጎኛል። በመጨረሻም ሁላችን ልናያት የምንጓጓውን እስራኤልን ራሱ ጌታ ተናግሮ በራሱ መንገድ እንድጎበኛት በማድረግ "ያከበሩኝን አከብራለሁ" የሚለውን ቃል በሕይወቴ ፈጸመው።

# ምዕራፍ ፳፯

## "ቃለ ሕይወት ሞተች" አለኝ ጌታ

*ጊዜው 1981 ዓ.ም ነው። ወንጌላዊ ኬዳሞ በጌጃ ቃለ ሕይወት እያገለገሉ 15 ዓመታት ያህል አለፏቸው። ጌጃም በብዙ አቅጣጫ ለፋች፣ አገልግሎቶችም በዙ፤ ሰዎችም ተቀያየሩ፤ አዳዲስ አጥቢያዎችም ከጌጃ መውጣት ጀመሩ። ከሁሉም በላይ የአገሪቱ ፖለቲካዊ መልክም መቀየር ጀመረ። የከፋው ስደት ቀንሶ አማኞች አንገታቸውን አቅንተው መንዝ ድምጻቸውንም ማሰማት ጀመሩ። በየዘመናቱ የሚገጥማቸው ስደት ከማዳከም ይልቅ የባሰ ያሳደጋቸው ቤተ ክርስቲያናትም በህቡዕ ከሚሠሩበት ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። ቃለ ሕይወትም የተዘጉባት አጥቢያዎች እየተከፈቱላት፣ በድብቅ የተዘራው በግልጽ እየበቀለላት በተለያዩ ስፍራዎች አጥቢያዎች ያሏት ትልቅ እና ጠንካራ ቤተ እምነት እየሆነች መታየት ጀመረች።*

*አንጋፋዋ የጌጃ አጥቢያም አገር አቀፉን የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት የሚመሩ መሪዎች አበርክታ የራሷን አሻራ በቤተ ክርስቲያኒቱ አስደናቂ እድገት ላይ ማሳረፍ ችላለች። እንደነ ወንጌላዊ ኬዳሞ ያሉት የአጥቢያይቱ አገልጋዮችም በመላ አገሪቱ ባሉት የቤተ ክርስቲያኒቱ አጥቢያዎች ሁሉ እየተዘዋወሩ የሚያገለግሉ እና የቤተ ክርስቲያኒቱን የአስተምህሮ አንድነት የሚያስጠብቁ ዘቦች ሆነዋል።*

*በእርግጥ ወንጌላዊ ኬዳሞ በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የእድገት ሂደት ውስጥ ከቀድሞም ጀምሮ በተለያዩ ዘርፎች የላቀ ተሳትፎ ነበራቸው። ገና በቀድሞው ዘመን ቃለ ሕይወት አሃዱ ብላ አንድ ማዕከላዊ መዋቅር ለመመስረት ስትነሳና የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር ሲቋቋም ኬዳሞ ለወንጌል አገልግሎት በዘመቱበት ዲላ ሆነው ከበርካታ አገልጋዮች ጋር የራሳቸውን ሃሳብ እና ምክር በመለገስ ለስኬቱ አስተዋጽኦ አድርገዋል። በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ምስረታ ለምንም የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ስያሜ ሲጸድቅ ከመስለሎቻቸው ከነ*

ወንጌላዊ መስፍን ተስፋዬ[2] ጋር በመሆን አብረው ወስነዋል። የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው የእምነት አቋም ሰነድ ተዘጋጅቶ በጠቅላላ ጉባኤ ጸድቆ ሥራ ላይ ሲውልም ኬዳሞ የዝግጅት ቡድኑን በሰብሳቢነት መርተዋል።

ወንጌላዊው በዚህ መልኩ በልዩ ልዩ ስፍራ እየዞሩ ያገለገሏትን የእግዚአብሔር መልካም አምላክነት ምስክር የሆነች ቤተ ክርስቲያንን በፍቅር ይወዷታል። በጌጃ ቃለ ሕይወት ሳሉም በመላ አገሪቱ የሚገኙ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ጥሪ ሲያቀርቡላቸው ነበር። የአገሪቱ ሁኔታ በተሻሻለ ቁጥርም ይህ የአገልግሎት ጥሪ እየጨመረ ሄዷል።

በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ ይሆን ያስተዋሉት ኬዳሞ የተለያዩ አገልጋዮች እንዲተኳቸው እና የጌጃ አገልግሎታቸውን እንዲረከቧቸው ጥረት ማድረግ የጀመሩት። በዚህ ወቅት ጌጃም ብዙ አገልጋዮችን በማፍራት ላይ ነበረች። በተለያየ ሁኔታ ከአገልግሎት በሚወጡ እና ከሌላ የአገልግሎት ኃላፊነት የተነሳ ጌጃን የሚለቅቁ አገልጋዮች በሌሎች እየተተኩ ነበር። በ1980ዎቹ መግቢያም አገልጋዮችን እንዲያፈሩ ከተቋቋመው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሽፈራው ፈይሳ እና ገብረ እግዚአብሔር ካህሳይ በዲፕሎማ ተመርቀው የኬዳሞ ረዳት በመሆን የሚሠሩ የወንጌል አገልጋዮች ሆነዋል።

በዚሁ ሁኔታ ውስጥ እያሉም በኬዳሞ ሕይወት አንድ ነገር ሆነ። በ1981 ዓ.ም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ምረቃ ተካሄደ። የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር የሆኑት ኬዳሞም ተመራቂዎችን አስመርቀውና የዕለቱ መርኃ ግብር በመልካም ሁኔታ ስለተጠናቀቀ ጌታን አመስግነው ወደ ቤታቸው አመሩ።

ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች የምረቃ በዓል የተከናወነበት የሳምንቱ መጨረሻ ቀን አልፎም አዲስ ሳምንት ተተካ። በአዲሱ ሳምንት ማክሰኞ ዕለትም ኬዳሞ እንደልማዳቸው በእኩለ ሌሊት ተነስተው ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ተገናኙ። የሌሊት ጸሎታቸውን እያደረሱ ስለምድራቸውና ስለቤተ ክርስቲያን እየማለዱ እያለም አንድ ድምጽ ወደ እርሳቸው መጣ። እግዚአብሔር በግልጽ «**ቃለ ሕይወት ሞተች!**" አላቸው።

---------------------//--------------------

[2] ወንጌላዊ መስፍን ተስፋዬ በኤስ አይ ኤም ትዘጋጅ የነበረችው ቃለ ሕይወት ጋዜጣ አዘጋጅ የነበሩና በጌጃ ምስረታ ወቅት በሽምግልና ሳይቀር አገልግለው ለአንጋፋው የቤተ ክርስቲያኒቱ የአምልኮ አዳራሽ ማሠሪያ የሚሆነውን ገንዘብ አሰባስበው ለተተኪ መሪዎች ያስተላለፉ ብሎም የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ስያሜ እና መዋቅር ሲበጅ የበኩላቸውን ተሳትፎ ያደረጉ ታላቅ የወንጌል አርበኛ ናቸው። ወ/ዊ መስፍን በኋለኛ ዘመናቸው በአስፈሪው የስደት ወቅት ሳይቀር በጽናት ወንጌልን የሰበኩ እና በብርሃን ወንጌል እና በመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያናት በመጋቢነት አገልግለው ያለፉ የኬዳሞ አጋር ታላቅ አገልጋይ ነበሩ።

እግዚአብሔር "ቃለ ሕይወት ሞተች" ብሎ ሲነግረኝ ለኔ በጣም አሳዛኝ እና አስደንጋጭ ስለሆነብኝ ነገሩ በልቤ ከብዶ ነበር የተሰማኝ። በእርግጥ እኔም በዚያ ጊዜ በየአካባቢው እየዞርኩ አገለግል ስለነበር ቤተ ክርስቲያናችን የነበረችበት ሁኔታ ፈጽሞ ደስ የሚያሰኝ ሆኖ አላገኘሁትም። በየአጥቢያው አንድ እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምሩቅ እና አስተማሪ ሆኖ ምዕመናኑን የሚያገለግል ሰው ማግኘት ብርቅ ነበር። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያንን ከሞት ለመታደግ የራሴን ጥረት ለማድረግ ወስኜ መንቀሳቀስ ጀመርኩ።

በ1982 ዓ.ም በስድስት የተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውሬ በርካታ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን አስተማርኩ። ዋና ርዕሴም ቤተ ክርስቲያን እንዳትሞት ተተኪ አገልጋይ ስለማፍራት፤ ተተኪ አገልጋይ በየአጥቢያው ሊዘጋጅ እንደሚገባና ልክ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንደተካ ሁሉ ቤተ ክርስቲያናት ተተኪ እንዲያዘጋጁ የ1ኛ ተሰሎንቄን መጽሐፍ በሙላ በአገሪቱ እየተዘዋወርኩ ሳስተምር ቆየሁ።

እኔ ደራርቤ ይዤአቸው የነበሩትን የጌጃ ልዩ ልዩ ኃላፊነቶችም ለመቀነስ ጥረት ማድረግ ጀመርኩ። በተለይ ከባድ ኃላፊነት ሆኖብኝ የቆየውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ዳይሬክተርነት ከኔ ጋር እያገለገሉ የነበሩት ሽፈራው ፈይሳ እና ገብረ እግዚአብሔር ካህሳይ እንዲረከቡኝ ለሽማግሌዎች ጥያቄ አቀረብኩ።

እነርሱ እኔን እንዲተኩ ስጠይቅም የመጀመሪያ ምክንያቴ እነዚህ ወጣቶች ያኔ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተምረው በማጠናቀቃቸው እውቀታቸውን የሚያካፍሉበት እድል ማግኘት ነበረባቸው። በዚያ ላይም ዘመኑ እየተሻሻለ ነው። እኔ ደግሞ እንግሊዝኛ መናገርና ኮምፒዩተር መጠቀም ስለማልችል ገብረ እግዚአብሔር እና ሽፈራው ግን ሁለቱም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችግር አልነበረባቸውም። ከውጪ ከሚመጡ ልዩ ልዩ አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር ብንፈልግ እኔ በአስተርጓሚ ለመጠቀም ስገደድ እነርሱ ግን በቀጥታ በእንግሊዘኛ መነጋገር ስለሚችሉ የመተካካቱ ሂደት ወሳኝ ነበር።

ከዚህም ባሻገር እኔ ለረጅም ጊዜ ሁሉን ነገር ጠቅልዬ ይዤ ብቆይ እና አንድ ቀን የሆነ ነገር ቢያጋጥመኝ አገልግሎቱ የሚጎዳ ሲሆን እነርሱ አገልግሎቱን ቢረከቡ ግን እኔ እዚያው በአማካሪነት ስለምኖር ችግር አይፈጠርም የሚል እሳቤ ነበረኝ።

ይህንን ሃሳቤን ሳቀርብላቸው ሽማግሌዎች በጉዳዩ ላይ አመኑበት። በዚሁ መሠረት ገብረ እግዚአብሔር ዋና ሽፈራው ደግሞ ምክትል ዳይሬክተሮች ሆነው ሥራውን ተረክበው ያከናውኑ ጀመር።

ይህም ለኔ ትልቅ እረፍት ስለሆነኝ እንደተመኘሁት በጌጃ ቃለ ሕይወት ባሉ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ፈቃድ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እየዞርኩ አገልጋዮችን ማሰልጠን እና ቤተ ክርስቲያናትን የማስታጠቅ አገልግሎቴን ቀጠልኩ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱን ሥራም ሙሉ በሙሉ ሳልተው በአማካሪነት እና አስፈላጊ

ሲሆንም በማስተማር እያገለገልኩ ቆየሁ። ይህ አገልግሎቱም ከጌጃ እስከተለየሁበት ጊዜ ድረስ ቀጥሎ ነበር።

ለጌጃ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እኔ ትልቅ ሸክም ስለነበረኝ በአማካሪነት ጊዜዬም ብዙ ምክር እሰጥ ነበር። እንዲያውም በ1987 ዓ.ም አቶ ጥላሁን ኃይሌ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሰብሳቢ እያለ እኔ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ ራሱን ችሎ በራሱ ቅጥር ግቢ ከቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ነጻ ሆኖ እንዲሠራ እና በአማርኛ ቋንቋ በዲግሪ አስተምሮ እንዲያስመርቅ ሃሳብ አቅርቤ ነበር። ይሁንና ይኸው ሃሳብ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ጉዳይ በእኔ ቤት በተካሄደ ስብሰባ ላይ ጸድቆ በአፈጻጸሙ ሂደት ላይ ምክክር እያደረግን እያለ እኔ ወደ ዋና ጽሕፈት ቤት እንድዛወር ተጠየቅሁ።

እግዚአብሔር "**ቃለ ሕይወት ሞተች!**" ብሎ ከነገረኝ አሳዛኝ መልዕክት አንጻርም በጌጃ እያለሁም ብዙ ጥረት ማድረጌን ቀጠልኩ። በተለይ በየቦታው እየዞርኩ የማየው አደገኛ ሁኔታ በጣም ያሳዝነኝ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ከአስጨናቂው የስደት ዘመን ስትሻገር ነገሩ ሁሉ መልኩን እየለወጠ ይሄድ ጀመር። ቃለ ሕይወት በየቦታው በሚነሱ ብዙ የስህተት ትምህርቶች እየተበዘበዘች ሄደች። እኔ ዞሬ አሠራራቸውን ሳይም በየቦታው ለእሁድ አምልኮም ሆነ ለሌሎች ፕሮግራሞች አገልጋዮች የሚጠሩት ከተለያየ ቦታ እና ከተለያየ ቤተ ክርስቲያን ነበር።

የሚጠሩት ወይም የሚጋበዙት አገልጋዮችም በየሄዱበት የሚናገሩት የየራሳቸውን አጀንዳ እና ዓላማ እንጂ የቃለ ሕይወትን አስተምህሮ እና ለቤተ ክርስቲያኑ የሚያስፈልገውን ጠቃሚ የወንጌል መልዕክት አልነበረም። በብዙ ቦታ አገልጋይ ሲጠሩም ሽማግሌዎች ጸልየው መክረው የወሰኑትን አይደለም። ተራው ምዕመን ሳይቀር ድንገት ያገኘውን ዝም ብሎ ያለ ዓላማ ይጋብዝ እና ቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ ያቆም ነበር። እግዚአብሔር የተናገረኝ የቤተ ክርስቲያን መሞት ጉዳይም በዚህ ሁሉ ሊገለጽ የሚችል ነበር። እኔም በየቦታው ሄጄ ሳይ ቃለ ሕይወት ባለቤት የሌላት ሆና ሊያገለግል የመጣው ሰውን ማንነት የሚመረምር እና "አንተ ማን ነህ? ከየት ነው የመጣኸው?" የሚል ሰው አልነበረም። አንድ ሰው የፈለገውን ካስተማረ በኋላም ‹ይህ ትምህርት እንዴት ነው?› ብሎ ሊገመግም እና ትክክለኛውን ከስህተት ለመለየት የሚጥር እረኛ አልነበረም።

እኔም በተሰበረ ልብ ችግሩን ለመቅረፍ ሁል ጊዜ መጸለይ እና ጌጃ የነበረኝን አገልግሎት ለሚረከበኝ ሰው አስተላልፌ በመላ አገሪቱ እየዞርኩ ለማገልገል እና መስመር የማስያዝ ሥራ ለመሥራት እመኝ ጀመር። ለእያንዳንዱ አጥቢያ ቢያንስ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ የተማረ አገልጋይ ያስፈልጋል ብዬም አንዲት አነስ ያለች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መምሪያ አዘጋጀሁ። እድሉን ባገኘሁበት ቦታ ሁሉ እየዞርኩም አንድ አስተማሪ የሚሆን ሰው ለአንድ አጥቢያ ለማዘጋጀት መጣር ጀመርኩ።

ያኔ አስቤ የነበረው በአንድ አጥቢያ አንድ መጋቢ እንዲኖር ማድረግ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ የተማረና በአጥቢያው ያሉትን ሊያስተምር የሚችል አንድ አገልጋይ እንዲኖር ለማድረግ መጣር ነበር። በዚህ ሃሳብ መሠረት በቦቢቻ፣ በዱራሜ (ጠዛ)፣ በአርሲ ነገሌ፣ በዱኒቃ፣ በኩየራ፣ ኩየአ (ሲዳማ ውስጥ) እየዞርኩ ሳስተምር ቆየሁ። በዚሁ ሁኔታ ቃለ ሕይወትን ለመታደግ በሙሉ ኃይሌ እዚህ እና እዚያ እየተሯሯጥኩ እያለም በትውልድ መንደሬ ሻሾጎ ባለችው በኖሻ ከተማ ለሁለት ጊዜያት ተመላልሼ የ፲ኛ ተሰሎንቄን መጽሐፍ ሳስተምር ቆየሁ። ይህንን ትምህርት ለማጠናቀቅም በአንድ ዓመት ውስጥ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ እዚያው አመራሁ።

# ምዕራፍ ፳፫

# እኔ ወደ ቦኖሻ ጌታ ግን ወደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ እና ካናዳ

## ጌታን መቅደምና በበሽታ መመታት

ወንጌላዊ ኬዳሞ "ቃለ ሕይወት ሞተች" የሚለውን የጌታን ድምጽ ከሰሙ ወዲህ እዚህም እዚያም ያለው የቤተ ክርስቲያን የተዘበራረቀ አስተምህሮ እና የቃለ ሕይወትን የቀደመ ቅዱስ ቃሉ ላይ ያተኮረ አካሄድ የዘነጋ አሠራር እንዲስተካከል ሲሯሯጡ እና የራሳቸውን ጥረት ሲያደርጉ ቆዩ። በዚህ መኃልም የትውልድ አገራቸው ሻሾን ወረዳ ዋና ከተማ ወደ ሆነው ቦኖሻ እየተመላለሱ ሲያገለግሉም ቆዩ። በዚሁ ጊዜ አንድ ሃሳብ መጣላቸው። "ቃለ ሕይወት እየሞተች እኔ ለምን አዲስ አበባ ዝም ብዬ እየጸለይሁ ብቻ እቀመጣለሁ? አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ፤ ጌታስ የተናገረኝ ለዚሁ አይደል?!" ብለውም አሰቡ። ወዲያውም በተደጋጋሚ የተመላለሱባትን እና የራሳቸው ወገኖች ያሉባትን ቦኖሻን ማዕከል አድርገው በመላ አገሪቱ በሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት እየዞሩ ቃለ ሕይወትን ከሞት የመታደግ አገልግሎት ሊሰጡ አሰቡ።

ይህንኑ ሃሳብም ለባለቤታቸው ወ/ሮ ታደለች አማከሩ። ወ/ሮ ታደለችም "እይ ዝም ብለን አንሄድም እግዚአብሔር ቦኖሻ ሂዱ ሲለን እንሄዳለን።" ብለው መለሱ። ኬዳሞ ደጋግመው ጉዳዩን ቢያነሱም ወ/ሮ ታደለች "እግዚአብሔር ሲናገረን እንሄዳለን።" በሚለው አቋማቸው ጸኑ። ኬዳሞም በባለቤታቸው ምላሽ ቅር በመሰኘት "አንቺ እንደ ሎጥ ሚስት ከተማ ወድደሽ አዲስ አበባ ለመቅረት ነው እንቅር የምትይው። ድሮም የሴቶች ችግር ይህ ነው። (አንድን ቦታ ከለመዱ ትተው ለመሄድ አይፈልጉም)" ብለው ባለቤታቸውን ወቀሱ። በጉዳዩ ላይም ሳይግባቡ በጭቅጭቅ ብቻ ነገሩን ቋጭተው ኬዳሞ በዚያው 1982 ዓ.ም ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ቦኖሻ ተጓዙ።

በእቅዳቸውም መሠረት ሐሙስ ሙሉ ቀን ሲያስተምሩ ከዋሉ በኋላ ዓርብ ጠዋትም በደንብ ተዘጋጅተው ወደ አገልግሎት ስፍራ ሄዱ። በዚሁ እለትም ከአገልግሎት በኋላ ምንም እንኳን የባለቤታቸውን ይሁንታ ባያገኙም በራሳቸው ውሳኔ ብቻ ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር በእርሳቸው ወደ ቦኖሻ የመዘዋወር እና ከቦኖሻ በመነሳትም

ወደ መላው ኢትዮጵያ እየተዘረጉ የማገልገል ሃሳባቸው ዙሪያ ምክክር ለማድረግ ቀጠሮ ይዘዋል።

ወንጌላዊው ፍጹም ጤነኛ ሆነው ወደ ቦኖሻ ያመሩ ሲሆን ዓርብ ጠዋት ደርሰው መድረክ ላይ እስኪወጡ ድረስ ምንም የሕመም ስሜት አልነበራቸውም። በድንገት ግን እዚያው መድረክ ላይ እየሰበኩ እያለ ከእግር ጥፍራቸው እስከ ራስ ጸጉራቸው ድረስ መላ ሰውነታቸውን ኃይለኛ ድንዛዜ ያዛቸው። ከውስጣቸው የሚሰማቸው ስሜትም ፈጽሞ ሊቆጣጠሩት ከሚችሉት በላይ ሆነባቸው። ፈጽሞ መንቀሳቀስ ስላልቻሉም የከዚህ ቀደምም ሆነ የበኋላ የአገልግሎት ሕይወታቸው አጋጥሟቸው በማያውቅ ሁኔታ በአቅራቢያ ላሉ አገልጋዮችን "ኑ ውሰዱኝ አልቻልኩም" አሉ። አገልጋዮችም ተሯሩጠው መጥተው አፋፍሰው ከመድረክ አወረዷቸው። ወዲያውም ባሳረፏቸው ስፍራ ላይ ሆነው በላይ በላይ ያስመልሳቸው ጀመር። ሀሞት እስኪወጣ ድረስም አስመለሳቸው። ለትንሽ ጊዜ ያህልም አረፍ ብለው ቆዩ። ትንሽ ነፍሳቸው መለስ ስትልላቸውም የቀድሞ ጥንካሬያው የተመለሰላቸው ስለመሰላቸው በዙሪያቸው ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባይቀበሏቸውም "የጀመርኩትን ትምህርት ልጨርስ" ብለው ወደ መድረክ ወጡ። ሆኖም አሁንም እንደቀድሞአቸው ጠንክረው ማስተማር አልቻሉም። ብቻ የጀመሩትን እንደምንም ጨርሰው ከእርሳቸው ሊማር በተሰበሰበው ሕዝብ ልብ ሀዘን እና ፍርሃት በሚለቅ ሁኔታ ከሚሰማቸው ሕመም እና ከድካማቸው ለማረፍ በሰዎች ተደግፈው ከመድረክ ተወሰዱ።

በሁኔታው የተደናገጡት የቦኖሻ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና አገልጋዮች ተሯሩጠው ኬዳሞን በቅርብ ወዳለችው ሃላባ ከተማ ወሰዷቸው። ከሃላባም በዚያው ዕለት ወደ ሻሸመኔ ሄዱ። ሕመማቸውም በጣም እየጸና ሄደ። ሻሸመኔ አቶ ኬዉሶ የሚባሉ አማኝ እና የራሳቸው መድሃኒት ቤት ያላቸው ሰው ቤት ለሦስት ቀናት ያህል ተኙ። ወደ ክሊኒክ ተወስደው ተመርምረውም "በጭንቅላታቸው ውስጥ ሁለቱን የአንጎላቸውን ክፍሎች የሚያገናኘው ሥር ደርቋል፤ ኸለዚህ ነው በጣም የሚያማቸው።" ተብለው ተመለሱ።

መድኃኒት አዋቂው ኬዉሶም ለሕመማቸው ተገቢ የሆነውን መድኃኒት አገኙላቸው። እርሱን እየተጠቀሙም ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ ለሦስት ወር ያህል ሕመምተኛ ሆነው አልጋ ላይ ውለው ራሳቸውን ሲያስታምሙ ቆዩ። በዚሁ ጊዜ 1983 ዓ.ም ገቡቶ ከጅማሬው አንስቶ እስከ ኅዳር ወር ድረስ ኬዳሞ ከአገልግሎታቸው ተለይተው ጊዜውን አልጋ ላይ አሳለፉ። በእነዚሁ ሦስት ወራትም ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል እየተመላለሱ ሕክምና ሲከታተሉ ነበር። ከዚህ ሁኔታ የተነሳም የታመሙበት እና የፈውሳቸው ጊዜ ረዝሞ ኅዳር ወር ሲገባ ወንጌላዊው "ለምን በበሽታ መታኸኝ? " ብለው በእግዚአብሔር ላይ በማዘን ውስጣቸውም ቁጣ፣ ምሬትና እና ቅሬታን ተሞላ።

ይህንን የአገልጋያቸውን የበረታ ሕመም እና ሃዘን የሞላበት ሁኔታ ያዩ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችም ወንጌላዊው እረፍት እና የጽሞና ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው አመኑ። አምስት መቶ ብር በመስጠትም ወደ ባቦጋያ (ደብረ

ዘይት) ሄደው እንዲያርፉ ነገሯቸው። ወንጌላዊውም በሽማግሌዎች በጎ ሃሳብ ተስማምተው ለ15 ቀናት ያህል ሊያርፉ እና ሊጸልዩ ወደ ባቦጋያ ሄዱ።

ኬዳሞ ባቦጋያ ደርሰውም እሮብ እና ሐሙስ ዕለትን በጸጥታ በሕመም የተዳከመ አካላቸውን እያሳረፉ ዋሉ። ዓርብ ዕለት ግን ከማለዳው 12:00 ሰዓት ጀምረው በጾም እና በጸሎት የእግዚአብሔርን ፊት ሲፈልጉ እና ውስጣቸው ያለውን ቅሬታ ለአምላካቸው ሲያጫውቱ አረፈዱ። ነገር ግን ብዙም ሳይቆዩ ልክ ዕኩለ ቀን ሲሆን በ6:00 ሰዓት ላይ እግዚአብሔር መልስ ሰጣቸው።

ለኬዳሞም "የእኔን ጊዜ ቀድመሃል" አላቸው። ወንጌላዊውም ወዲያው በጸጸት በአምላካቸው ፊት አነቡ። የእግዚአብሔርን ጊዜ በትዕግስት ለመጠበቅ ተስማሙና በኃዘን የተኮማተረው ልባቸው ተፈትቶ ወዲያውም ሰላማቸው ተመለሰ። የንስሃ እና የምስጋና ጸሎት አድርሰውም ተነሱ። እግዚአብሔር በተናገራቸው ጉዳይ ዙሪያ ለመዘርጋትም ጌታ የወሰነው ጊዜ እስኪደርስ እና የእርሱ ፈቃድ እስኪፈጸም መጠበቅ እንዳለባቸው ተረዱ። ለ15 ቀናት ተብሎ የተያዘው የእረፍት እና የጽሞና ጊዜም የልቦና እረፍታቸውን በጥቂት ቀናት ውስጥ አግኝተው ወዲያው ቅዳሜውን ወንጌላዊው ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ሕመማቸውም በዚያው ወር ከላያቸው ላይ ተነሳ።

በዚያው የኀዳር ወር ማብቂያ ላይም በአንድ ዕለት የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ የሆኑት ዶ/ር ሙላቱ ባፋ ወንጌላዊ ኬዳሞን ለመጠየቅ ወደ ቤታቸው አመሩ። ወደ ኬዳሞ ቤት ያመሩት ዋና ጸሐፊ ወንጌላዊውን በቤታቸው አግኝተዋቸው አንድ አዲስ ዜና ነገሯቸው።

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ ቦርድ ኤስ. አይ. ኤም በሚዘጋጅ የአገልግሎት እና ቤተ ክርስቲያኒቱን የማስተዋወቅ ጉዞ ላይ ቤተ ክርስቲያኒቱን በመወከል ሁለት ሰዎች እንዲሄዱ ውሳኔ አሳለፈ። ወንጌላዊ ኬዳሞ ከሌላው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አንጋፋ የወንጌል አገልጋይ እና የእምነት አባት አቶ መርኪና መጃ ጋር በመሆን በጥር ወር ቤተ ክርስቲያኒቱን ወክለው ወደ ውጪ አገራት እንዲጓዙ ተመረጡ። ዶ/ር ሙላቱም ይህንኑ የሁለቱን አገልጋዮች ቃለ ሕይወትን በመወከል ወደ አሜሪካ፣ ካናዳ እና እንግሊዝ የመጓዝ ዜና ለወንጌላዊው በዚያች ማክሰኞ ዕለት ሲያበስሩ ወንጌላዊው እንደልማዳቸው "እሺ፣ ጸልዬ መልስ እሰጣለሁ።" አሉ።

ኬዳሞ ከዚያች ዕለት ምሽት ጀምሮም በጉዳዩ ላይ መጸለይ ጀመሩና ጸልየው ወደ መኝታቸው ሄዱ። በዚያው ሌሊትም አንድ ራእይ አዩ። በራእዩ ውስጥ ኬዳሞ በሻሾጎ ምድር ድሮ የሚያውቋቸውና የአክስታቸው ባል የነበሩ ግለሰብን እና ወንድማቸውን አዩ። እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች ከሞቱ የቆዩ ሰዎች ነበሩ። በሕልማቸው ውስጥም ሁለቱ ሰዎች በታጠረ የከብት በረት ውስጥ ሆነው ኬዳሞ ደግሞ ከውጪ ቆመው ወንጌልን ሲሰብኩላቸው ራሳቸውን አዩ።

*ወንጌላዊው ይህንን እንግዳ የሆነ ሕልም እንዳዩ ከእንቅልፍ ነቁ። ወዲያውኑ ያዩትን ሕልም ለባለቤታቸው ለወ/ሮ ታደለች ተረኩላቸው። ወ/ሮ ታደለች ወንጌላዊው ከሞቱ የቆዩትን የአገራቸውን ሰዎች በሕልም ማየታቸውን አስበው "አዬ ያንተ ነገር! በቃ ከሞቱትም ይሁን ካሉት ጋር ሁል ጊዜ ሻሸን ነው።" ብለው ቀለዱ። ኬዳሞም በነገሩ ከልባቸው ሳቁና ባልና ሚስቱ በተፈጠረው አጋጣሚ እየተሳሳቁ ነገሩን ችላ ብለውት መልሰው ተኙ።*

*ይሁንና ወንጌላዊው በጠዋት የማለዳ ጸሎታቸውን እየጸለዩ እያለ ነገሩ በራላቸው። ልክ በሕልም እንዳዩአቸው ሰዎች በአሜሪካ፣ በእንግሊዝ እና በካናዳ ክርስትና ሞቷል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የእነዚህ አገራት ክርስቲያኖች በዓለማዊነት ሕይወት ዙሪያቸውን ታጥረዋል። ለእነዚሁ ሰዎች ወንጌልን ለመስበክ መሄድ እንዳለባቸውም ኬዳሞ ወዲያው ተረዱ። ይህንኑ ያዩትን ሕልም ከነፍቺው ሄደው ለቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ሙላቱ ባፋ በመናገር ለመጓዝ ፈቃደኛ መሆናቸውን አሳወቁ።*

*ጥር 1983 ዓ.ምም ወንጌላዊ ኬዳሞ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን በመወከል ከአቶ መርኪና መጃ ጋር ወደ ተጠቀሱት አገራት በረሩ።*

---------------------//--------------------

## አሜሪካ፣ ካናዳና እንግሊዝ

እግዚአብሔር ሻሸጎ ገብቼ ልቀመጥ እያልኩ የነበርኩትን ሰው ጌታ መክሮ እና በሕመም ከተኛሁበት አልጋ ላይ አስነስቶ በጥር ወር ከሌላው የቤተ ክርስቲያናችን ትልቅ አገልጋይ አቶ መርኪና መጃ ጋር ወደ አሜሪካ ላከኝ። እኔም በአሜሪካ ላሉ ክርስቲያኖች የማስተላልፈውን መልእክት ከእግዚአብሔርና ከላከችኝ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተቀብዬ በደንብ ተዘጋጅቼ ውቅያኖስ አቋርጬ ለመብረር አውሮፕላን ተሳፈርኩ።

በጉዞአችን ወቅትም ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ተነስተን ወደ ጀርመን በማምራት የጥቂት ጊዜ ቆይታ አድርገን አውሮፕላን በመቀየር አትላንቲክን ተሻግረን አሜሪካ ገባን። አሜሪካ እንደደረስንም ጉዞአችን በሦስት ወራት ውስጥ በትላልቆቹ የአሜሪካ እና የካናዳ አገራት ልዩ ልዩ ከተሞች እና በእንግሊዝ ጭምር ወደሚገኙ በርካታ ቤተ ክርስቲያናት እንድንሄድ ፕሮግራም የተያዘልን መሆኑ ተነገረን።

እኔና አቶ መርኪና በሄድን በማግስቱ የተጓዝንበትን ተልዕኮ ለመጀመር በ12:00 ሰዓት ሪፖርት እና መልእክት ለማቅረብ ተዘጋጅተን እንድንወጣ ተነግሮን ወደ ማደሪያችን ገባን። እኛም በጉዞ የደከመ አካላችንን ለማሳረፍ ወዲያውኑ እራታችንን በልተን ተኛን። ተኝተን ትንሽ እንደቆየንም አቶ መርኪና ከተኛበት ተነስቶ ሰዓት ሲያይ 12:00 ሰዓት ይላል። ወደ እኔ መጥቶም "ኬዳሞ ተነስ ነግቷል" አለኝ። እኔም በጠዋት ሪፖርት እና መልእክት አቅራቢ ስለሆንኩ ተደናግጬ ተነሳሁ። እርሱም የምንበላው እዚያው

የምናድርበት ቤት ተቀምጦልን ስለነበር ሁሉን በፍጥነት አዘገጃጅቶ ቁርሳችንን በላን። ከዚያም ወደ ውጪ ለመውጣት መንጋቱን ብንጠብቅ ብንጠብቅ አይነጋም። እኔም ሁኔታውን አይቼ "አረ ጋሽ መርኪና ጊዜው ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ሳይሆን አይቀርም ተሳስተናል።" አልኩት።

ከዚያም የሰዓቱን ነገር ትተን "በቃ በአገሩ ወፍ ካለ ሲነጋጋ ይጮኻል" አልኩት እና ተመልሰን መንጋቱን ለመጠባበቅ ያህል ብለን ተኛን። ብዙ ሰዓት ከተኛን በኋላ ሲነጋ ወፍ ጮኸ እና ተነሳን። ለካስ እኛ የሰዓቱን መለዋወጥ ሳናውቅ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ነበር የተነሳነው። በኋላም ስድስት ሰዓት ያህል ቆይተን በትክክለኛው ማለዳ 12 ሰዓት ተነሳን። በዚህ ሰዓት ከተነሳን በኋላም አቶ መርኪናን "አሁን ሌሊት በበላነው ቁርስ እንሂድ ወይስ ደግመን እንብላ?" አልኩት። ሁለታችንም በተፈጠረው አጋጣሚ እና በራሳችን ላይ ስቀን አቶ መርኪና ምግብ ማዘገጃጀት በደንብ ስለሚችል በፍጥነት አቀራርቦ በዚያው ዕለት ሁለተኛውን ቁርሳችንን በልተን ወጣን።

በዚያ ማለዳም ሄደን የቤተ ክርስቲያናችንን ሪፖርት እና የመግቢያ መልእክት ከትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ አንብቤ አቀረብኩ። ይሁንና አገሩ ከእኛ አገር ጋር ካለው የሰዓት ልዩነት አንጻር ጨለማው አልፎ ንጋት ላይ ብንሆንም እኔ ቀን ይሁን ማታ ያሰንበት ሰዓት አልገባኝም ነበር። ከመልእክቱ በኋላ ግን "በቃ ለምሳ እንሂድ!" ሲሉን ቀን እንደሆነ ገባኝ፤ ሄደንም ምሳችንን በላን። ምሽት ላይ ወደ እራት ወስደውን እያለም ሰዓቱ አሳስቶን ሁለት ጊዜ ቁርስ እንደበላን ነግረን አሳቅናቸው።

በአሜሪካ እና በተቀሩት አገራት በነበረን ቆይታም በኢትዮጵያ ሲያገለግሉ ቆይተው ወደ አገራቸው የተመለሱ ከእኔ ጋር በቢሮ የሠሩና ለዓመታት ዓለቃዬ የነበሩት እነ ማ/ር ዳይን የመሰሉ የቀድሞ ሚሲዮናውያን ስለነበሩ እነርሱ በብዙ ነገር ይረዱንና በምንሄድበት ሁሉ አብረውን በመጓዝ ያስተረጉሙልን ነበር። እኛን ወደ አሜሪካ የጋበዙን የኤስ አይ ኤም ቢሮ ሲሆን በአሜሪካ፣ በካናዳ እና በእንግሊዝ ባሉ ልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያናት በመዘዋወርም ስለ ቤተ ክርስቲያናችንና ከኤስ አይ ኤም ጋር ስላላት ግንኙነት መናገር ይጠበቅብን ነበር።

የኛ ጉዞ እና አጠቃላይ ፕሮግራማችን ለአሜሪካውያን፣ ለካናዳውያን እና ለእንግሊዛውያን የየአገሩ ቤተ ክርስቲያናት እንጂ ከራሳችን አገር ሰዎች ጋር ወይም ከእነርሱ ቤተ ክርስቲያናት ጋር ምንም ፕሮግራም የተያዘለት አልነበረም።

እኛ አሜሪካ በሄድንበት ወቅት ደግሞ በኢትዮጵያ ያሉ የጌጃ መሪዎች እና የኛ ወዳጆች እነ ጋሼ ላቀው ወደ ልጆቻቸው እና ወደሚያውቋቸው ወዳጆቻቸው መሄዳችንን እና ሻርለት የሚባል ቦታ እንዳለን ነግረውን ነበር። እኛ አሜሪካ እንደገባንም የኛን እዚያ መድረስ የሰሙ ሁሉ ስልካችንን አፈላልገው ይደውሉልን ጀመር። ገና እንደገባንም በአንድ ሌሊት ሰባት ጊዜ የተለያዩ ኢትዮጵያውያን እየደወሉ ሰላም እያሉን እነርሱንም እንድንጎበኝ ጠየቁን። እኛም ሁኔታውን ከሚያስተናግዱን እና ከሚመሩን ሰዎች ጠይቀን መልስ ልንሰጥ ቀጠሮ ሰጥተን ተለያየን።

እኔም ነገሩን በማግስቱ ለኛ ፕሮግራም አስተባባሪዎች በጥያቄ መልክ አነሳሁ። ከሚ/ር ዳይ እና ከሚ/ር አንደርስ ጋር አብረን በሆንንበት ሰዓት "እንዴት ነው የኛ ቆይታ እና የተያዘው ፕሮግራም? ከፈረንጆች ጋር ብቻ እንድንገናኝ እና እንድናገለግል ነው ወይስ ኢትዮጵያውያንን ማግኘትንም ይጨምራል?" ብዬ ስጠይቃቸው ፕሮግራሙ ለፈረንጆች ብቻ እንደሆነ ነገሩኝ።

እኔም በነገሩ ቅር ተሰኝቼ ወዲያውኑ "እኔ ምንም ትልቅ ሰው አይደለሁም። ነገር ግን እግዚአብሔር በኔ ተጠቅሞ ከሠራው ሥራ የተነሳ የብዙዎች አባትና ወንድም ሆኛለሁ። እዚህ ብዙ ቤተሰብ አለኝ። ታዲያ እነዚህን ሰዎች ሳላገኝ ከተመለስኩ ፈጽሞ አሜሪካ መጥቻለሁ ማለት አልችልም።" ስላቸው በሁኔታው ተደናገጡ። ከዚያም ተማክረው በዚያ ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወደነበሩበት ዋሺንግተን (ምንም እንኳን እዚያ ለፈረንጅ ቤተ ክርስቲያን የተያዘ ምንም ፕሮግራም ባይኖርም) ኢትዮጵያውያኑን ብቻ ለማግኘት እንድንሄድ በፕሮግሙ ላይ አካተቱ፤ የኛን ሙሉ ወጪ ሸፍነውም ጉዞውን አመቻቹልን።

ከዚህም ሌላ እኛ የምንሄድባቸው የአሜሪካም ሆነ የካናዳ አስቴቶች ከመሄዳችን በፊት በዚያ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያናት መልእክት እንዲደርሳቸው እና እንዲዘጋጁ አደረጉ። ለእኔም በሄድኩበት ሁሉ ኢትዮጵያውያን ካሉ አንድ ቀን ከእነርሱ ጋር እንድውል እና እንዳስተምር ፕሮግራም ተዘጋጀልኝ። በዚህ ዓይነት ሁኔታም እነርሱ አስቀድመው ካወጡት ፕሮግራም ውጪ ወደ ዋሺንግተን ብቻ ስንሄድ የተቀሩትን ግን በቀጥታ በፕሮግራሙ መሠረት እየሄድን ኢትዮጵያውያንና ፈረንጆችንም አገለገልን። እግዚአብሔር በጣም ረድቶንም ምንም ሳንቸገርና አንድም ፕሮግራም ሳይደናቀፍ በሦስቱ አገራት ተዟዙረን በሦስት ወራት ውስጥ 77 ጊዜ ያህል መልዕክት ያቀረብኩኝ ሲሆን ከዚህ ውስጥ አስራ አራቱን ብቻ ለኢትዮጵያውያን በአማርኛ ሰበክሁኝ።

ይህ ሁሉ ሲሆን በመጀመሪያ ጊዜ ከጓጠመን የሰዓት መዛባት አስቂኝ ገጠመኝ ሌላ የገጠመን የከፋ ችግር አልነበረም ይሁንና እኔ በአንድ ሆቴል የአሳማ ስጋ በልቼ ጨጓራዬን በመታመሜ ከዚያች ዕለት በኋላ የአሳማ ስጋ መብላት በሙተዋ በድጋሚ ሳያመኝ የውጪ አገራት ቆይታችን ተጠናቀቀ።

በዚህ ጉዞአችን ወቅት በጉዞው ዋና ዓላማ መሰረት በመልእክቱ ውስጥ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እንዴት በኤስ. አይ. ኤም ሚስዮናውያን ጅማሬዋን እንዳገኘች፤ መቼ እንደተመሰረተች እና አሁን ምን ያህል እንዳደገች፤ ባሳለፈቻቸው የዕድገት ዓመታትም ምን ያህል በመከራ፣ በስደት፣ በእስራት፣ በመዘጋት እና በሞት አደጋዎች መካከል እንዳለፈች፤ በመጨረሻም የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ጽሕፈት ቤት ቢሮ በአሁን ወቅት ኮንቴይነር ውስጥ እንደሆነ እና ይህን መሰል ቤተ ክርስቲያኒቱ ያሉባትን ችግሮች አቀርብ ነበር። ከዚያም በኋላ ከ30-40 ለሚሆኑ ደቂቃዎች ስብከቴን አቀርባለሁ። እነ ሚ/ር ዳይም እኛ ስንናገር በማስተርጎም ያግዙን ነበር።

ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር አስቀድሞ በራእይ በተናገረኝ መሠረት እንዴት በአውሮፓ እና በአሜሪካ ክርስትና እየሞተ እንዳለ፣ አማኞች እንዴት በዓለማዊነት እንደተያዙ እና ከዚህ እንዲወጡ የሚያሳስብ መልእክት አቀርብ ነበር። በሄድንበት ቦታ ሁሉ አብዛኛው ሕዝብ መልእክታችንን በእምባ እና በለቅሶ ንስኃ እየገባ ነበር የተቀበለው። ከአገልግሎት በኋላም መጋቢያኑ እኛ ያደግነው ልክ እንደ እናንተ ባለ ሁኔታ እየተሰበክን ነው። አሁን ግን እኛ እንደዚህ መስበክ አንችልም እያሉ ያዝኑ ነበር። እኛም እንደታዘብነውና የሚያሳዝነው እውነታ በሦስቱ አገራት በአብዛኛው በቤተ ክርስቲያን የሚሰበሰቡት አረጋውያን እና ሴቶች ሲሆኑ ወጣቶች በጣም ጥቂቶች ነበሩ።

ቶሮንቶ በነበረን አገልግሎት በትልቅ የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ አዳራሽ ብዙ ሕዝብ ነበረ። በዚያ ጉባኤ እንዳየሁት አንዳንድ ወጣት ሴቶች በጣም አጭር ቀሚስ ለብሰው በጸሎት ሰዓት ሳይቀር ማስቲካ እያኘኩ ነበር የሚጸልዩት። እኔም በዕለቱ እየሰበክሁ የነበረው ስለ ቅድስና ስለነበር ከዚያ ጋር አያይዤ "በእግዚአብሔር ቤት ወደ እግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ እንደዚህ ለብሶ መምጣት አይገባም ይህ ራቁትነት ነው። ማስቲካ እያኘኩ መጸለይስ ልክ ነውን? እውነተኛ ጸሎትስ ነውን? በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር ጋር የልብ ግንኙነት ማድረግ ይቻላልን?" በማለት ጠንከር ያለ የግሳጼ መልእክት አስተላለፍኩ። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ መሬት ሁሉ እየወደቀና እያለቀሰ ነበር ንስኃ የገባው። እግዚአብሔር በዚያ ጊዜ በዚያ ሕዝብ ልብ ውስጥ ትልቅ ሥራ ሠርቷል።

እንግሊዝ አገር ስናገለግልም እንዲሁ እግዚአብሔር እንደተናገረን እውነቱን እንነግራቸው ነበር። አንድ ቀን በነበረኝ የስብከት ክፍለ ጊዜ የክርስቶስ እና የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ምን እንደሆነ በመግለጽ "ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ተልዕኮዋን ጥላለች። ብዬ አንድ ምሳሌ ነገርኳቸው። በአገሬ አንድ አካባቢ እያገለገልኩ እያለ ሁለት የማውቃቸው ሴቶች በተመሳሳይ ጊዜ የተወለዱ ልጆች ነበሯቸው። በኋላም እነዚሁ ልጆች አንዱ ሦስት ዓመት እስኪሞላው ድረስ በደንብ ጠንክሮ መሮጥ ሲችል ሌላው ግን እግሩ አልጸና ብሎ ሽባ ሆኖ መነሳት ተሳነው። እናቲቱም ብዙ ሃኪም እና ወጌሻ ጋ ወስዳው ምንም መፍትሔ አላገኘችም። ልጁ ዝም ብሎ ተቀምጦ ነበር የሚለው። በመጨረሻም እናቲቱ ምንም የሚረዳ መፍትሄ ስታጣ አንድ ቀን ቢላዋ አግላ የልጇን መቀመጫ ጠበሰችው። ከዚያ በኋላ ልጁ መቀመጥ አቃተውና ወንበር ምናምን እየያዘ እንደምንም ብሎ ይቆም ጀመር። ትንሽ ቆይቶም በራሱ መራመድ እና መሄድ ቻለ።"

"እናም እግዚአብሔር እናንተንም እንዲሁ ይጠብቃችኋል። እናንተ ያላችሁበት ሁኔታ ተመችቷችሁ ሽባ ሆናችሁ መቆምና መሮጥ አቅቷችኋል። በዚህ ላይ እናንተ ወንጌልን ለአፍሪካ እናደርሳለን ትላላችሁ፣ ነገር ግን የእናንተ የኋላ በር ክፍት ነው። እናንተ ወንጌል ወዳልደረሰበት ወደ ፊት ስትሄዱ፣ ወደ ቤታችሁ ክህደት፣ ዓለማዊነትና ሥጋዊነት በጓሮ በር ገብተዋል።" እያልኩ ስሰብክ እነርሱም ልክ እንደ ሌሎቹ በእግዚአብሔር ፊት እየወደቁ አልቅሰዋል።

እግዚአብሔር እኛን እዚያ የወሰደን ለፈረንጆቹ እንድንሰብክ እና እንዲባረኩ ብቻ ሳይሆን ለቃለ ሕይወትም ብዙ በረከት ያስገኘበት ነበር። ለዋና ጽሕፈት ቤት ሕንጻ ማሠሪያ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ፣ ለልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች የዲግሪ እና የዲፕሎማ ፕሮግራሞች መምህራንን ለመላክና በገንዘብ ለመደገፍ በብዙ ቦታ ቃል ተገብቶልን ነበር። በአሜሪካ በተለያዩ አምስት ቦታዎችም (እንደ ኮሎምቢያ የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም ባሉት ስፍራዎች) ስብሰባ አድርገናል። ካናዳም እንዲሁ የተሰበሰብን ሲሆን ሰዎችን ወደ አሜሪካ ከሚጠሩ ይልቅ አሜሪካ ለአንድ ሰው በሚያወጡት በአገር ውስጥ ብዙ ሰው ማስተማር (መርዳት) እንደሚችሉ ተነጋግረናል። እግዚአብሔርም ረድቶን በስብሰባዎቹ ላይ ብዙ መልካም ውሳኔዎችን አሳልፈናል።

በአሜሪካን ቆይታዬ ከቁሳቁስና ከገንዘብ አንጻር ለእኔ የሚሆን ነገር ለማግኘት ምንም ጥረት አላደረግሁም ነበር። ነገር ግን ለቮልስ ዋገን መኪናዬ የሚሆን አገር ውስጥ የጠፋ የመለዋወጫ ዕቃ ለመግዛት አስጽፌ ይገፔ ስለነበር እርሱን ገዛሁና ክፍያውን ለመግገፕ ካዘጋጀሁት ዶላር ላይ አውጥቼ ልከፍል ስል ሚ/ር ዳይ ራሳቸው ከፍለው እኔ እንዳልከፍል አድርገዋል።

ከዚህ ባሻገር ከፈረንጆቹ ጋር ስንገናኝ ስለ እኛ የግል አገልግሎት ሁኔታ እና ስለሚያስፈልጉን ጉድለቶቻችን ምንም አልተናገርንም። ስለ ቃለ ሕይወት እና ኤስ. አይ. ኤም የተናገርነው ግን በሄድንበት ሁሉ የሕዝቡን ልብ የነካ እና ቤተ ክርስቲያናቱ ስለ ኤስ. አይ. ኤም እና ቃለ ሕይወት ለመጀመሪያ ጊዜ በደንብ ሰምተው ያወቁበት ጊዜ ነበር።

ከዚህ ሌላ ወደ ኢትዮጵያውያን ስንሄድ በየደረስንበት በጣም አስደናቂ አቀባበል ይደረግልን ነበር። እኔን እንደ አባት የሚያዩኝ በርካታ መንፈሳዊ ልጆቼ በየቦታው እየተቀበሉ ያስተናግዱን እና በጣም ይንከባከቡን ነበር። ለምሳሌ፦ አንዲት ሣራ ባህታ የምትባል በጊኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ያስተማርኳት እህት አሜሪካን አግኝታኝ ነበር። ሣራ (አሁን ወደ ጌታ ሄዳለች።) ያኔ በጣም አስተዋይ የነበረች እህት ስትሆን ገና ከጊኛ ተለይታ ወደ አሜሪካን ለመሄድ ስትነሳ ከቤተ ክርስቲያን የመሸኛ ደብዳቤ አስጽፋ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የተማረችበትንም ተገቢ ማስረጃ ይዛ ነበር የሄደችው። በአሜሪካን ምድር ሣራ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነበረች። እኔ ወደ አሜሪካ በሄድኩበት ጊዜም በቤቷ የተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት አባላት የሆኑ አማኞችን ሰብስባ ሰው ሁሉ እርሷ ጋ አድሮ እነ እንድርያስ ሀዋዝ እና ሌሎች ብዙ ሰዎች መጥተው በእነርሱ ቤት አስተምሬአቸዋለሁ። በጊዜው ከአገራቸው ተለይተው ላሉት ለእነዚህ ወገኖች ያስተላለፍኩት ከጌታ የተቀበልኩት መልዕክት "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ..." በሚለው በማቴዎስ ወንጌል ላይ ያለውን ሃሳብ ነበር።

“ከአገራችሁ ተለይታችሁ በስደት የምትኖሩት ሕይወት በጣም ከባድ ቢሆንም ጌታ ወደ እኔ ኑ እንዳላችሁ በሙሉ ልባችሁ ወደ ኢየሱስ ብትጠጉ እና ከኢየሱስ ጋር ብትሆኑ ግን ሰማያውያን ትሆናላችሁ።” እያልኩም አስተማርኳቸው።

በዚህ ዓይነት በልዩ ልዩ ቦታዎች ስንዘዋወር መምጣታችንን ሰምተው የተዘጋጁ ኢትዮጵያውያን በጠሩን ቦታ ሁሉ እየሄድን ጌታ የሰጠንን መልዕክት ስናቀርብ ከረምን።

የአሜሪካ፣ የካናዳና የእንግሊዝ ቆይታችን እንዲህ ደስ የሚያሰኝ እና በብዙ በረከት የተሞላ ሆኖልን በክብር ከቦታ ቦታ ተዘዋውረን ያገለገልንበት ነበር። በሄድንባቸው ቦታዎች ሁሉ ሁኔታዎቹ ምቹ የነበሩ ቢሆንም የአገሩ የአየር ሁኔታ ከኛ አገር በጣም የተለየ ነበር። እኔ ግን ስለ አገሩ አስቀድሜ ሰምቼ ስለነበር በደንብ ተዘጋጅቼ ነበር የሄድኩት። አንድ ጊዜ ካናዳ እያለን ካሮላይና ወደሚባል አካባቢ እና በአሜሪካ እና ካናዳ መኃል ወዳለ የሀይቅ ዳርቻ ሚ/ር እስቴንሲንግ ከሚባሉ ሰው ጋር ሄድን። በዚያ ወቅት የአየሩ ሁኔታ በጣም ከባድ ቅዝቃዜ ያለበት በረዶ የሚወርድበት ጊዜ ስለነበር ኃይለኛ ብርድ ነበር።

እኔም ከዚህ ቀደም እስራኤል በሄድኩ ጊዜ ጌጃ ማታ ማታ ሳስተምር ልለብሰው በውድ ዋጋ የገዛሁት ካፖርት ስለነበረኝ እርሱን ለብሻለሁ። ከዚህም ሌላ አሜሪካ ከመሄዴ በፊት ታምሜ እያለ የሹራብ ሥራ የሚሠራ ሙሉጌታ የሚባል የጌጃ አባል የሆነ ወንድም የሹራብ ኮፍያ (ፊትን ሸፍኖ አንገት ድረስ የሚወርድ) እና ጓንት ሰጥቶኝ ስለነበር እሱን በደንብ አድርጌያለሁ። አቶ መርኪና ግን ምንም ሳያደርግ ወደሚጎበኘው ቦታ ሄድን። በጣም የሚገርመው ከዚህ በፊት ለሰባት ቀናት በቆየንበት የአሜሪካ ግዛት በእኛ አገር የሌለ ዓይነት ኃይለኛ ሙቀት እና ጸሓይ ነበር ያጋጠመን። እናም እንዲህ ዓይነት ቅዝቃዜ ሊኖር እንደሚችል ፈጽሞ አልጠበቅንም ነበር።

በዕለቱ ልክ እዚያ የሀይቅ ዳርቻ እንደደረስን አቶ መርኪና ያለ ኮፍያ እና ጓንት ሲወጣ በ15 ደቂቃ ውስጥ ብርዱ መላ ሰውነቱን ሲያቀዘቅዘው የሚይዝ የሚጨብጠውን አጣ። እጁን ኪሱ ሲከት ጭንቅላቱ በረዶ ይሆናል። በእጁ ጭንቅላቱን ሊሸፍን ሲሞክር እጁን ገና ከኪሱ ሲያወጣ በረዶው ያደርቀዋል። ይህን ያዩት እነ ሚስተር እስቴንሲንግ ተሯሩጠው ወዲያውኑ ካፖርት፣ ኮፍያ እና ጓንት ገዙለትና ችግሩ ተፈታ። በዚህ ላይም እዚያ በቆየንባቸው ቀናት አንዳንድ ቦታ አልጋው ራሱ ሙቀት የሚሰጥ ሽቦ ከውስጡ ስላለው እርሱ ያሞቀናል። አንዳንዱ አልጋ ላይ ደግሞ ፍራሹ ውስጡ ሙቅ ውሃ የያዘ ነበር። እናም በዚህ ዓይነት አስቸጋሪውን ስፍራ ምቹ አድርገውት ስለሚኖሩ እኛም ሳንቸገር ቆየን።

በእውነት በዚያ ጉዞ በነበረን ቆይታ ኤስ. አይ ኤሞች እኛን በታላቅ የክብር አያያዝ ነበር ያቆዩን። ሁል ጊዜ ከቤት ስንወጣ ታጥበን እንወጣ የነበረ ሲሆን በቀን ሦስት ጊዜ በጣም ጥሩ ሳሙናዎች እያገኘን እንታጠብ ነበር። በጉባኤ መካከል ስንቆም ሙቀቱ ላብ እንዳይፈጥርብን እና ሌላ ጠረን እንዳይኖረን በደንብ ታጥበን ተዘጋጅተን እንሄድ ነበር።

በአሜሪካ፣ በካናዳ እና እንግሊዝ ያየናቸው ሰዎች ሁሉ መልካም ሆነው ነበር ያገኘናቸው። እነርሱ በጣም የሰለጠኑ በመሆናቸው እኛ እንደርነሱ ለመሆን ብዙ ዓመታት ያስፈልጉናል። ጠንካሮችና ትጉዎች ስለሆኑ ሁሉን አመቻቹ እንጂ ያየነው አገር ከእኛ ጋር ሲነጻጸር የአየር ሁኔታው መቅሰፍት የሆነ አገር ነው። ክረምቱም በጋውም በጣም አስቸጋሪ ነው። ሰዉ ግን ሁል ጊዜ ሰውን ለመርዳት ይፈልጋል። በዚያ ላይም በነዚያ አገሮች ያለው እድገት በኔ አገላለጽ ሰው ለሚጠይቀው የአኗኗር ጥያቄ ሁሉ መልስ የተሰጠበት ነው።

እግዚአብሔር እኔን ከከብቶች በረት አንስቶ በእነዚህ ታላላቅ አገሮች አዟዙሮ፣ በታላላቅ ጉባኤዎች፣ በታላላቅ ሕዝብ እና የተማሩ ሰዎች ፊት ስለ እርሱ ሥራ እንድናገር አደርጎኛል። በእነዚህ ታላላቅ እና ኃያላን አገሮች ተዟዙሬን ስናገለግል ቆይተንም ከቀን ወደ ቀን የጦርነት ወሬ እያየለ ወደ መጣባትና ለውጥ ወደ ምትሸተው አገራችን በሰኬት ተመለስን።

--------------------------//--------------------------